የፖለቲካ ሥርዓት

Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com

ለሕዲሪኢ ምሥረታ
የሰው ኃይል ሥልጠና የተዘጋጀ

ታህሣሥ 1978
አዲስ አበባ

የፖለቲካ ሥርዓት

ለሕዲሪኢ ምሥረታ
የሰው ኃይል ሥልጠና የተዘጋጀ

ታህሣሥ 1978
አዲስ አበባ

መግቢያ፤-

በአብዮታችን ሂደት ውስጥ የአዲሱን የፖለቲካ ስርዓት ምስረታ ዕውን ለማድረግ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አመራርና በአብዮታዊው መንግሥት እንደዚሁም በሕዝባዊ ድርጅቶችና በመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ሰፊ አብዮታዊ ክንዋኔዎች እየተካሄዱ ናቸው። በተለይም ከኢሠፓ ምሥረታ ወዲህ በአንድ ዓመት ሁለገብ የአመራር ሰጪነት ሚናው የተገኙትን ባለ ብዙ ዘርፍ ውጤቶችን ስንመለከት የአዲሱ የፖለቲካ ስርዓት ምሥረታ በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መቋቋም የበለጠ እየተቃረበ መሄዱን እንገነዘባለን ።

ለአዲሱ የፖለቲካ ስርዓት መመስረት አንዱ ዓይነተኛ ማረጋገጫ የሰፊው ሕዝብ ሙሉ ሥልጣን መገለጫ የሆነው የኢ.ህ.ዲ.ሪ. መንግሥት ምሥረታ እንደመሆኑ መጠን የሪፐብሊኩን ምሥረታ ተግባራዊ ለማድረግና ሰፊው ሕዝብ ለወደፊት የሚደነግገው የኢ.ህ.ዲ.ሪ መንግሥት ሕገ መንግሥት መሠረት በመንግሥቱ አመሠራረት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ለማድረግ ከወዲሁ በቂ ዝግጅት መደረግ እንዳለበት አያጠያይቅም ።

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢ.ህ.ዲ.ሪ መንግሥት ምሥረታ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግና ስልጣኑን የሚወክሉት የተለያዩ የኢ.ህ.ዲ.ሪ የስልጣንና የአስተዳደር አካላት ውስጥ በምርጫ የሚሰይማቸው ግለሰቦችም የተጣለባቸውን ታሪካዊ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችሉ ስለ ሪፐብሊኩ ምንነት ፣ ዓላማ ተግባሮችና እንቅስቃሴያቸ ይዘት እንዲያውቁ የሚያስችላቸውን የስልጠና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል ።

የዚህም ጽሑፍ አብይ ዓላማ ሰፊውን ሕዝብ ለኢ.ህ.ዲ.ሪ.ምሥረታ ለማዘጋጀት በኢ.ሠ.ፓ. አመራር በሚከናወነው ሰፊ የስልጠና ተግባር ውስጥ የፖለቲካ ስርዓትን ምንነት ፣ ባህሪያት ፣ አካላትና ተግባሮችን በማመልከት አንዳንድ መሠረታዊ ሐሳቦችን በማስጨበጥ በዚህ ረገድ የሰፊው ሕዝብ ንድፈ ሃሳባዊ

ግንዛቤ ከፍ እንዲል መጠነኛ እገዛ ማድረግ ነው ።

ስለፖለቲካ ስርዓት ብዙ መጻፍና ሰፊ ሐተታ ማቅረብ እንደሚቻል ግልጽ ነው ። የዚህ የስለጠና ጽሑፍ መሠረታዊ ዓላማ ግን ከላይ ባጭሩ እንደተገለጸው የፖለቲካ ሥርዓትን ምንነት ፣ ተግባሮች ፣ አካላትን እንደዚሁም አመጣጡን በማመለከት አንዳንድ መሠረታዊ ንድፈ ሃሣባዊ ማጠቃለያዎችን ማቅረብ ይሆናል ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የፖለቲካ ስርዓትን መሠረታዊ ትርጉም ጠባዮችን ልዩ ልዩ አካላቱንና በአካላቱ መካከል የሚኖረውን ውስጣዊ ግንኙነት በአጭሩ ከተመለከትን በኋላ የፖለቲካ ስርዓትን አመጣጥ ፣ ተግባር ፣ ዕድገቱን አጠር ባለ መንገድ በመተንተን በሕብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ውስጥ በኢ.ሠ.ፓ መሪነት በመመስረት ሂደት ላይ የሚገኘው አዲሱ የፖለቲካ ስርዓት ምን መልክ ሊኖረው እንደሚችል ባጭሩ እንመለከታለን ።

2. የፖለቲካ ስርዓት ትርጉም

ስለ ፖለቲካ ስርዓት ምንነት በዝርዝር ለማጥናት እንድንችል ይህ ጽንሰ ሃሣብ የሚገለጽባቸውን ቃላት ማለትም ፖለቲካ እንደዚሁም ስርዓት የተሰኙ ቃላት ምን ማለት እንደሆኑ ባጭሩ እንመልከት ።

“ ፖለቲካ ” የተሰኘው ቃል በጥሬ ትርጉሙ ሲታይ “ ፖለቲክስ” ከተሰኘ የላቲን ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም በአማርኛ ሕዝብ ማለት ነው ።[1] በቀን ተቀን አጠቃቀሙ ደግሞ ይህ ቃል በብዙዎች ዘንድ አስጸያፊ ትርጉም እንዳለው ተደርጎ ይወሰዳል ። ለምሣሌ በቀደመ አበዎች በሀገራችን ውስጥ እከሌ ፖለቲካ ተናገርክ ተብሎ ታሰረ ” ወይም ” እከሌ ቁም ነገር ያለው ወሬ አያውቅም ዝም ብሎ ቦተሊካ ይናገራል ” የሚሉ አባባሎችን ሳንሰማ አንቀርም ። አልፎ ተርፎም ፖለቲካ ማለት ሰውን በነገር ማወናበድ ወይንም በመንግሥት ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት እንደሆነ አድርገው የሚገምቱ ጥቂቶች አልነበሩም ።

ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ትርጉሙ አንፃር ግን "ፖለቲካ" የተሰኘው ቃል ወይንም ጽንሰ ሃሳብ ከላይ ከተጠቀሱት የቀን ተቀን አጠቃቀሞች ሰፋ ያለ ትርጉም ያለው ቃል ነው ::

"... ፖለቲካ በመደቦች በማህበራዊ ቡድኖች እንደዚሁም በሕዝቦች መካከል የሚኖር አንድ ዓይነት ግንኙነትን የሚያመለክት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከስልጣን ወይም ከኃይል ጥያቄ ጋር በቅርብ የተያያዘ ትርጉም ያለው ቃል ነው ::"[2]

ፖለቲካ አንዱ የማህበራዊ ንቃተኅሊና ቅርጽ ነው :: እንደ ማህበራዊ ንቃተ ኅሊና ቅርጽነቱ ደግሞ የተመሠረተበትን የኢኮኖሚ ግንኙነት ዓይነት ወይንም የኢኮኖሚ መሠረት ያንፀባርቃል ::

በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ ፖለቲካ ባንድ መልኩ በሌኒን አገላለጽ "የተጠቀለለ የኢኮኖሚ ነፀብራቅ"[3] ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ የተለያዩ የሕብረተሰብ መደቦች የየራሳቸውን መደባዊ ጥቅም ለማስከበር በምሁራኖቻቸው አማካይነት በሚቀርጿቸው የፖለቲካ ርዕዮተዓለሞች ይገለጻል :: ከዚህም በላይ በመደቦች መካከል በሚካሄደው የመደብ ትግል ውስጥ የፖለቲካ ትግል ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል :: የዚህም መሠረታዊ መግለጫ የፖለቲካ ትግል ከፖለቲካዊ ስልጣን ጥያቄ ጋር በቅርብ የተያያዘ ከፍተኛው የመደብ ትግል ቅርጽ መሆኑ ነው ::

በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ የፖለቲካ በተለይም የፖለቲካ ትግል ይዘት የሚወሰነው መደቦች የየራሳቸውን የመደብ ጥቅም ለማስከበር በሚያቀርቡትና ጥቅማቸውም በሚያንፀባርቅበት ርዕዮተዓለም ነው :: ጨቋኝና ተጨቋኝ መደቦች በሚገኙበት የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ/ለምሳሌ በፊውዳሉ ስርዓትና በካፒታሊስቱ ስርዓት/ ውስጥ ገንኖ የሚታየው ርዕዮተዓለም በኢኮኖሚና በፖለቲካ የበላይነት ያለው መደብ ርዕዮተዓለም ነው :: ፖለቲካ ደግሞ የነዚሁ መደቦች ርዕዮተዓለም ተግባራዊ መግለጫ ሲሆን የገዢው መደብ ጥቅሞቹን ለማስከበር በሚያቀርባቸው የጥቅም ማስጠበቂያ ልዩ

ልዩ ድርጅታዊ ተቋሞች አማካይነት በተግባር ላይ ይውላል ። የገዥው መደብ የራሱን መደባዊ ጥቅም እንደሕብረተሰቡ አጠቃላይ ጥቅም አድርጎ በሚያቀርብባቸው የፕሮፖጋንዳና የቅስቀሳ መሣሪያዎቹ አማካይነት /ለምሣሌ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች / የራሱን የመደብ ጥቅም ለማስፈጸም ይሞክራል ።

ፖለቲካ የላዕላይ መዋቅሩ አካል አንደ መሆኑ የሚወሰነው በተመሠረተበት የኢኮኖሚ መሠረት ላይ መሆኑ ቢታወቅም በኅብረተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ የፖለቲካ ግንኙነቶች ይዘት ከኢኮኖሚው መሠረት በተጨማሪ በተለያዩ የሕብረተሰብ ቡድኖች ፣ በግለሰቦች ጥቅም እንደዚሁም በየሀገሩ ታሪክ ፣ ባህልና ወግ ሊወሰን የሚችል መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ።[4] ፖለቲካ ባንድ መልኩ ከአንድ መንግሥት የፖለቲካ ዓላማ ፣ ተግባርና ከሌሎቹም የማህበራዊ ስርዓቱ አካላት ጋር የሚኖረው ግንኙነት ይወስናል ። ፖለቲካ የተመሠረተበትን የኢኮኖሚ ግንኙነት በቀርብና በቀጥታ ያንፀባርቃል ቢባልም ከተመሠረተበት የኢኮኖሚ መሠረት አንፃራዊ ነፃነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው ። የዚህም ዋና ምክንያት የኢኮኖሚ ዕድገትን በሚገዙ የኢኮኖሚ ሕጎችና የሕብረተሰብን የፖለቲካ ዕድገት በሚገዙ ሕጎች መካከል ያለው ነባራዊ ልዩነት ነው ።

ከዚህ በላይ የፖለቲካን ምንነትና መሠረታዊ ትርጓሜ ባጭሩ ለመቃኘት ሞክረናል ፤ ዋናው ዓላማችን የፖለቲካ ስርዓትን ምንነት መመርመር ስለሆነ ይኸው ፅንሰ ሃሣብ የሚገለጽበትን ሁለተኛውን ቃል ማለትም "ስርዓት" የተሰኘውን ቃል ምንነት ባጭሩ እንመልከት ።

"ስርዓት" የተሰኘው ቃል በቀን ተቀን አጠቃቀሙ ደንብ፣ ሕግ ወዘተ... የሚል ትርጓሜ ይዞ ይገኛል ።[5] አከሌ ስርዓት አያውቅም " ፣ " ድርጊቱ ሁሉ ከስርዓት ወጪ ነው " የሚሉ አባባሎች በብዙዎች ሰዎች አነጋገር ውስጥ የሚዘወተሩ ናቸው ።

•ስርዓት የተሰኘው ቃል ግን ከቃሉ ተራ አጠቃቀም ሰፋ ያለ ጽንሰ ሃሣብ ያዘለ ቃል ነው ።

እስቲ በዙሪያችን የሚገኙትን ልዩ ልዩ ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ ክስተቶችን አተኩረን እንመልከት ። በዙሪያችን የምንመለከታቸው ሰዎች ፣ ልዩ ልዩ እንስሳት ፣ ዛፎች ወዘተ... በተበታተነ መልክ ያሉና በመካከላቸውም ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለ መስለው ይታዩናል ። በርግጥ ላይ ላዩን ብቻ ለተመለከተ ሰው ሁኔታው ከላይ የተጠቀሰውን ለመስል ይችል ይሆናል ። ትክክለኛው ሁኔታ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው ።

በዙሪያችን የሚገኙ በአጠቃላይም በዓለም ዙሪያ ያሉ ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ ክስተቶች ሁሉ የተበታተኑና ጨርሶ የማይገናኙ ሳይሆኑ እርስ በርስ የተያያዙና የተወሰነ የአደረጃጀት ቅርጽ ይዘው ይገኛሉ ፣ ሰዎች ሁሉ በተወሰነ ቤተሰብ ወይንም ብሔረሰብ ወይንም መደብ ወይንም በተወሰነ የዜግነት ክፍፍል ተደራጅተው ይገኛሉ ፣ እንስሳትም የተወሰነ ዘር ፣ ዓይነት ወይንም ደረጃ ይዘው የሚገኙ ናቸው ። ግማሾቹ ይበራሉ ፣ ግማሾቹ በውሃ ውስጥ ይኖራሉ ግማሾቹም ደቃቅና በዓይናችን እንኳ ልናያቸው የማንችላቸው ናቸው ። ታዲያ ሁሉም የተወሰነ የተቀናጀ ስነሕይወታዊ አደረጃጀትና ክፍፍል አላቸው ። ሁሉም የተዋሃደው የሁለንተናዊው ዓለም ስርዓት አካላት ናቸው ። በዓለማችን ዙሪያ ማናቸውም ተፈጥሮአዊ ወይንም ማህበራዊ ክስተት አንዱ ካንዱ ፍጹም በሆነ መልክ ተገንጥሎ ወይንም ተለይቶ አይገኝም ።

ለምሳሌ በገጠር መንገዶች ላይ የሚሽከረከር አንድ ጋሪ እንውሰድ ። ይህ ጋሪ ሁለት ጎማዎች ፣ መቀመጫ ፣ ጋሪውን ከፈረሱ ጋር የሚያያይዙ ሁለት የእንጨት ወይንም የብረት ዘንጎች ፣ እንደዚሁም ጋሪውን የሚጎትት ፈረስና ፈረሱ በተመደበለት አቅጣጫ መንቀሳቀሱን የሚቆጣጠር የጋሪ ነጂ አለው ። እንግዲህ ይህ ጋሪ አንድ ራሱን የቻለ የተዋሃዱ አካላት ያለው ስርዓት ነው ማለት ነው ። የዚህ ጋሪ ተግባር የተሰራበትም ዓላማና ጠቅላላ እንቅስቃሴው የሚወሰነው በጋሪው አካላት መካከል ባለው ጤናማ ግንኙነትና ውህድነት ነው ። ከጋሪው አካላት መካከል አንዱ ቢጎድል ወይንም እንከን ቢኖረው ጋሪው ሊንቀሳቀስ አይችልም ። የስርዓትም መሠረታዊ ትርጉም ከዚሁ ምሳሌ ጋር ተዛምዶ ያለው ነው ።

ማናቸውም ስርዓት /የተፈጥሮ ፣ የሕብረተሰብ ፣ ሰው ሠራሽ/ በአንድ ወጥ መንገድ የተደራጀና የተዋሐደ የነባራዊው ዓለም አካል ነው ::

ለምሣሌ መሬትን የወሰድን እንደሆነ ባንድ በኩል ሌሎች ፕላኔቶችና ከዋክብት ጨረቃ ጭምር የሚገኙበት የሶላር ሲስተም አካል ስትሆን በኛ ሶላር ሲስተም ውስጥ ካሉት ሌሎች ፕላኔቶች አንዷ ናት ::

በአማርኛ "ሥርዓት" የምንለው ቃል በእንግሊዝኛ ቋንቋ "ሲስተም" ለተሰኘ ቃል የተሰጠ ትርጉም ሲሆን "ሲስተም" የተሰኘውም ቃል "ሲስቴማ" የግሪክ ቃል የተገኘ ነው::[6] ትርጉሙም አንድ የተለያዩ አካላት ያለው የተዋሐደና የተጠቃለለ ነገር ወይንም ክስተት ማለት ነው ::

አሌክሳንደር ስፒርኪን የተባለው ዕውቅ የሶቪየት የፍልስፍና ተመራማሪ ስርዓት ለሚለው ቃል የሰጠው ዲያሌክቲካዊ ማቴሪያሊስት ትርጉም :-

> "ስርዓት ማለት አንድ ውስጣዊ ድርጅት ያለውና አካላቱ በጥብቅ የተሳሰሩና በአንድነት ተጠቃልለው የሚንቀሳቀሱ ከውጪ አካላት ጋር ካላቸው ግንኙነት አኳያ በጥብቅ ተሳስረው የሚገኙ አካላትን ያዘለ ነው "[7] ይላል ::

ማናቸውም ስርዓት /ማህበራዊም ይሁን ተፈጥሮአዊ ወይንም ፖለቲካዊ / ስርዓቱን የሚያቀናጁ ወይንም የሚያዋቅሩ አካላት ይኖሩታል :: እያንዳንዱ የስርዓቱ አካል በስርዓቱ ውስጥ የተለያዩ ተግባሮችን ያከናውናል :: እነዚህ ተግባሮች ደግሞ ፍጹም የተለያዩ ሳይሆኑ ውስጣዊ ግንኙነት ያላቸውና ለስርዓቱ ሕልውና አስፈላጊ የሆኑ ናቸው :: የያንዳንዱ የስርዓቱ አካል ባህሪይ እንዱ ካንዱ ሊለያይ ቢችልም ስርዓቱን ባዋቀሩት አካላት መካከል በሚኖረው ግንኙነትና መተሳሰር የቴነሳ ስርዓቱ

ባጠቃላይ የሚይዘው ባህርይ ከአካላቱ የተለየና ቋሚ የሆነ ነው።
እያንዳንዱ ስርዓት አንድ ወጥ የሆነ የተዋሃደ አካል ይፈጥራል ይሁን እንጂ ማናቸውም ባጋጣሚ በድንገት የተዋሐዱ የአካላት ስብስብ አንድን ስርዓት አያስገኝም ማናቸውም ስርዓት የሚፈጠረው ስርዓቱን በሚያዋቅሩ አካላት መካከል ቋሚ ፣ የረጋ ፣ የተደጋገመና አስፈላጊ የሆነና ለስርዓቱ ሕልውና ወሳኝነት ያለው ግንኙነት ፣ አንድነትና መተሳሰር ሲፈጠር ብቻ ነው ።

ማናቸውም ዓይነት ስርዓት የየራሱ መዋቅር አለው ። ይህም በስርዓቱ አካላት መካከል የሚኖረውን የግንኙነት ዓይነት ይወስናል ። ከዚህም በተጨማሪ የስርዓቱን ጥንቅር ፣ ተግባርቅንና ባህሪያቱን ይወስናል ።[8] በስርዓቱ ላይ የሚካሄደው ማናቸውም ዓይነት መዋቅራዊ ለውጥ በስርዓቱ መሠረታዊ ባህርይ ላይ ለውጥ ማስከተሉ የማይቀር ነው ።

ስለማናቸውም ዓይነት ስርዓት /ለምሣሌ ስለ ተፈጥሮ ፣ ስለ ኢኮኖሚ ፣ ስለ ባህል ስለ ፖለቲካ ስርዓት /ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖረን የሚቻለው በመጀመሪያ የስርዓቱን መሠረታዊ ፍሬ ነገር ማለትም ከሌሎች ስርዓቶች የሚለዩትን መጠናዊና ዓይነታዊ ባህርያቱን በግልጽ ለማወቅ ስንችል ነው ። ለምሣሌ የካፒታሊስቱ ስርዓት ከሌሎች ስርዓቶች ሁሉ ዓይነተኛ የሚያደርገው በኢኮኖሚ አስተዳደርና አደረጃጀት ረገድ በካፒታሊስቱ የእሴት ሕግ ላይ መመስረቱ ነው ። ከዚህም በላይ የማናቸውም ስርዓት መለያ ባህርይ የስርዓቱ ጥንቅር ነው ። ይህም ማለት ስርዓቱን የሚያዋቅሩ አካላት ምንነት ማለት ነው ። ቀደም እንደተጠቀሰው ከዚህም ሌላ ስለማናቸውም ስርዓት የሚኖረን ግንዛቤ ስለስርዓቱ መዋቅር በሚኖረን መሠረታዊ ዕውቀት ላይ የሚመሠረት ነው ። ለምሣሌ የማናቸውም ማህበራዊ ስርዓት መዋቅር የሚወሰነው በስርዓቱ ውስጥ ገኖ በሚታየው የምርት ግንኙነት ዓይነት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ስርዓትን በማመልከት አንድ መነሣት ያለበት መሠረታዊ ነጥብ ማናቸውም ዓይነት ስርዓት በዕድገት ደረጃው ከርሱ በላይ ላለው የስርዓት ዕድገት ደረጃ እንደ

ስርዓቱ አካል ሆኖ የሚታይ ሲሆን በዕድገት ደረጃው ከርሱ በታች ላሉ አካላት ደግሞ እንደ ስርዓት ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል ። ስለሆነም በስርዓትና በስርዓት አካላት መካከል ያለው ግንኙነት አንፃራዊ ነው ።

ለምሣሌ የካፒታሊስት ሕብረተሰብን ማህበራዊ ስርዓት ብንወስድ በውስጡ የካፒታሊስቱን ስርዓት ኢኮኖሚ ፣ ፖለቲካ ፣ የሕግ ስርዓት አካላት ያሉት ሲሆን ከዚህ ውስጥ የካፒታሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት በራሱ እንደ አንድ ስርዓት ወስደን ብናየው በውስጡ የቡርዧዊውን መንግሥት ፣ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ተቋሞችን ለምሣሌ ፓርቲያችንና የሙያ ማህበራትን እንቅስቃሴ አካቶ የሚገኝ መሆኑን እንገነዘባለን ።

ሌላ ምሣሌ እንውሰድ ። ለምሣሌ ቀኝ እጃችንን ብንመለከት አምስት ጣቶቻችንን እናገኛለን ። በእጃችን የምናደርገው እንቅስቃሴ /ለምሣሌ መጻፍ ፣ መጨበጥ ፣ ምግብ መጉረስ / የአምስቱን ጣቶቻችንን የተቀናጀ እንቅስቃሴ ይጠይቃል ። ከነዚህ ጣቶች መካከል ባንዱ ጣት ጉዳት ቢደርስ በእጃችን የምናከናውነው ሥራ የተጓለሰ ይሆናል ። የያንዳንዱ ጣት ተግባር አንዱ ካንዱ የተለየ ቢሆንም ለምሣሌ አመልካች ጣት ፣ የቀለበት ጣት /ወዘተ... የሁሉም ጣቶቻችን የተጣመረ ግልጋሎት በእጆቻችን ለምናደርገው የመጨበጥ ፣ የመጻፍ የማመልከት ፣ የመብላት የማጠብ ወዘተ. እንቅስቃሴ አስፈላጊ መሆኑን እንገነዘባለን ። የስርዓትን ምንነት ፣ በስርዓትና በአካላቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ከዚህ ምሣሌ ጋር በማገናዘብ ለንረዳ እንችላለን ።

እነሳሳችን የፖለቲካ ምንነት ለመረዳት እንድንችል ጽንሰ ሃሣቡ የሚገለጽባቸውን ቃላት በቅድሚያ መረዳት በመሆኑ የፖለቲካ ና የስርዓትን ምንነት ባጭሩ ለመመልከት ሞክረናል ። በዚሁ የጽንሰ ሃሣቦች ግንዛቤ ላይ በመመስረት የፖለቲካ ስርዓትን ምንነት ለመመርመር እንሞክር ።

የፖለቲካ ስርዓት የማህበራዊ ስርዓት መዋቅር አካል ነው ። የፖለቲካ ስርዓትን ከሌሎቹ የማህበራዊ ስርዓት አካላት

ልዩ የሚያደርገው የበላይነቱ ነው ። የፖለቲካ ስርዓት ሕብረተ ሰቡ ውስጥ ላዕላይ ስልጣን ያለው አካል ነው ። የፖለቲካ ስር ዓቱ የሚያስተላልፋቸው ሕጎች ፣ ደንቦችና ሌሎች ድንጋጌዎች ሁሉ በሌሎች የማህበራዊ ስርዓት አካላት ዘንድ የግዴታ ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው ።9

የፖለቲካ ስርዓት ጽንሰ ሃሣብ ከመንግሥት መሠረታዊ ጽንሰ–ሃሣብ እንደዚሁም ከሕብረተሰብ የፖለቲካ ድርጅቶች ጽንሰ–ሃሣብ ሰፋ ያለ ነው ። በእርግጥ የሕብረተሰቡ መሠረታዊ ዓላማ ዎች ተግባራዊ የሚሆኑትና ለነዚህም ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ፖለቲ ካዊ ፖሊሲዎችና ሕጎች የሚወጡት በሕብረተሰቡ የፖለቲካ ድርጅቶች አማካይነት ነው ። ይሁን እንጂ የፖለቲካ ስርዓትን ጽንሰ ሃሣብ ወይንም ፍሬ ነገር ወደ ፖለቲካዊ ድርጅቶች ደረጃ ብቻ ዝቅ አድ ርጐ መረዳት ስህተት ነው ። የፖለቲካ ስርዓት ከሕብረተሰብ የፖ ለቲካ ድርጅቶች ተግባሮች የሰፋ ትርጉም ያለው ጽንሰ ሃሣብ ነው።

የፖለቲካ ስርዓት ከፖለቲካ ድርጅቶች በተጨማሪ ፖለቲካ ዊና ሕጋዊ የምግባረ ስብዕ ደንቦችን ፣ በሕብረተሰቡ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ማህበራዊ ቡድኖችና ልዩ ልዩ ተቋሞች መካከል የሚታዩትን ፖለቲካዊ ግንኙነቶችንና እነዚህንም ግንኙነቶች የሚ ገዙትን ታሪካዊ ርዕዮተ ዓለማዊ ባህላዊና ሕጋዊ ደንቦችን ሁሉ የሚያቅፍ ነው ።

3. የፖለቲካ ስርዓት አነሳስና ዕድገት

የፖለቲካ ስርዓት አመጣጥ ከሕብረተሰብ ፖለቲካዊ አደረ ጃጀት ጋር ተያይዞ መታየት አለበት ። ይህ ደግሞ በሕብረተሰብ ዕድገት ተከታታይ ታሪክ ውስጥ ከመደቦች መፈጠርና ከመደብ ጥቅም ማስከበሪያ ማህበራዊ ተቋሞች መከሰት ጋር ተያይዞ መታየት ያለ በት ጉዳይ ነው ።

ሕብረተሰብን በተለያዩ መንገዶች ከፋፍሎ ማጥናት ይቻ ላል ። ለምሣሌ በዕድሜ እንደዚሁም በፆታ እየከፋፈልን ልናጠና እንችላለን ። ይህ ዓይነቱ አከፋፈል በሰው ሥነ ሕይዎታዊ

የተመሠረተ ነው ። በሌላ በኩል ወይንም ቴሪቶሪያል ክፍፍል ላይ
ወይንም በነገድ በብሔር ወይንም በብሔረሰብ ወይንም ደግሞ ሕብረተሰብን
በቀዳሚ/ፕሪሚቲቭ/ እየከፋፈልን ለናጠና እንችል ይሆናል ። ዳሩ ግን ስለ ሕብረተሰብ ምንነት ፣ አደረጃጀትና ዕድገት ትክክለኛ ግንዛቤ ማግኘት የምንችለው የሕብረተሰብን ዕድገት በተለይም የሕብረተሰብ ፖለቲካዊ አደረጃጀት መሠረቶችን በትክክል ለማወቅ የምንችልበትን የሕብረተሰብ ዕድገት ማቴሪያሳዊ መሠረቶችን በጥልቀት ስንመረምር ነው ።

ሕብረተሰብን በተለያዩ መንገዶች ከፋፍሎ ማጥናት ቢቻልም የተሟላ የሕብረተሰብ ዕድገት ግንዛቤ ማግኘት የምንችለው ቀደም እንደተጠቀሰው የሕብረተሰብ ዕድገት ማቴሪያሳዊ መሠረቶችን በተለይም የመደቦች አመጣጥና ክፍፍልን በጥልቀት ስናጤን ነው ። የሕብረተሰብ የፖለቲካ አደረጃጀት መሠረት ከመደቦች መከሰትና ከመደብ ክፍፍል መታየት ጋር ተገናዝቦ የሚታይ ሲሆን የመደብ ክፍፍል ደግሞ በሕብረተሰብ ማህበራዊ ግንኙነቶች የተለያዩ ዘርፎች ላይ /ለምሣሌ ማቴሪያሳዊ ፣ ርዕዮተዓለማዊ/ ከሚያሳድረው ተፅዕኖ አኳያ መታየት የሚገባው ነው ።

የመደቦች አመጣጥ ክፍፍል በጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ ከታየው የሥራ ክፍፍል መበራከትና ከሥራ ምርታማነት ማደግ እንደዚሁም ከጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጣዊ ክፍፍልና በየጊዜው ከተካሄዱት የጉዛ ግጭቶች ውጤት ሲሆን በዚሁ ምክንያት ቀደም ሲል በጎሣ ወይንም በዘር ዝምድና ላይ ተመስርቶ የነበረው የሕብረተሰብ አደረጃጀት በመደብ ክፍፍል ላይ በተመሠረተ የሕብረተሰብ አደረጃጀት ሊተካ ችሏል ። ይህም ሲባል በሕብረተሰቡ ውስጥ ቀደም ሲል የታየው በዘር ዝምድና ላይ የተመሠረተው ማህበራዊ ግንኙነት ጨርሶ ተደምስሷል ማለት አይደለም ።

የመደቦች መከሰትና የመደብ ትግል በተወሰነ የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ መታየት በሕብረተሰብ ማህበራዊ አደረጃጀትና አወቃቀር ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል ። ቀደም ሲል በጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ ያልተለመደና ያልታዩ አዳዲስ

የሕብረተሰብ የማህበራዊ ግንኙነቶች ዓይነቶች /ለምሳሌ ፖለቲካዊ ፣ ሕጋዊ ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ወዘተ./ ሊከሰቱ ችለዋል :: በሕብረተሰብ የማህበራዊ ኑሮ ዕድገትም ውስጥ ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ ጥቅም ማስከበሪያ አዳዲስ ማህበራዊ ተቋሞች ተከሰቱ :: ከነዚህም ማህበራዊ ተቋሞች መካከል የዋነኛነትን ስፍራ ይዞ የሚገኘው መንግሥት ነው :: መንግሥት በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ የተከሰተ በኢኮኖሚና በፖለቲካ የበላይነት ያለው መደብ የፖለቲካ ስልጣን ማስከበሪያ መሣሪያ ነው ::

መንግሥት የፖለቲካ ሥልጣን ማስከበሪያ መሣሪያ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም የፖለቲካ ስርዓት የሚያቅፈው መንግሥትን ብቻ ሳይሆን ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ፣ የልዩ ልዩ መደቦች የተለያዩ ጥቅሞች ማስከበሪያ የሆኑትን ሕዝባዊ ድርጅቶችንና መሰል ተቋሞችን እንደዚሁም ሕጋዊና ፖለቲካዊ ንቃተ ኅሊናንም ጭምር የሚይዝ ነው ::

በጨቋኝና ተጨቋኝ መደቦች በተከሰቱበት ሕብረተሰብ ውስጥ የሕብረተሰብ የፖለቲካ አደረጃጀት ከፍተኛ ዕድገት ያሳየው በካፒታሊስቱ ስርዓት ማህበር ውስጥ ነው :: ቀደም ሲል በፊውዳሉ ስርዓት ውስጥ በተለያዩ ሀገሮች በተመሠረቱ የተበታተኑ የፊውዳል ግዛቶች ምትክ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ላይ የተመሠረቱ በተለይም በኢንዱስትሪ በዳበሩ ሀገሮች ውስጥ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ በተካሄዱት የቡርዧዋው አብዮቶች ማግሥት በቡርዣዋው መደብ የበላይነት ላይ የተመሠረቱ ብሔራዊ የቡርዧዋ መንግሥታት ተመሠረቱ :: በተለይም የቡርዧዋው መደብ ፊውዳላዊ የዘሩን አስተዳደርን ገርሰስ በመጣል በምትኩ " በእኩልነት ፣ በወንድማማችነትና በሕብረት" ስም የራሱን መደባዊ አስተዳደር ለመሠርት ቻለ ::

ከዚህም በላይ በየዘመኑ የነበሩ የቡርዧዋው የፖለቲካ ተንታኞችና ምሁራን መንግሥትን ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ያቀረቧቸው የፖለቲካ ንድፈ ሃሣቦች የቡርዧዋውን የፖለቲካ ስርዓት ለማጠናከር ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር ::

ለምሣሌ የፈረንሳዮን የፖለቲካ ምሁር የዣን ዣክ ሩዘን/1789-
1778/ የሶሺያል ኮንትራት ንድፈ ሃሣብ ፣ የሞንቴስኪን
/1689-1775 / የስልጣን ክፍፍል ንድፈ ሃሣብ ፣ የጆን
ሎክንና /1632-1704/ የሌሎችንም የቡርዧዋ ምሁራን አስተ
ዋጽኦ መጥቀስ ይቻላል ። እነዚህ ምሁራን ለቡርዧዋው መደብ
መንግሥት መመስረትና ለቡርዧዋው የሕግና የርዕዮተ ዓለም ስር
ዓት መጠናከር ያበረከቱት አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ እንደነበር
ከዓለም ታሪክ ሂደት ልንገነዘብ እንችላለን ።

ስለ ቡርዧዋው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን አመሰራረት በተ
ለይም ስለ ቡርዧዋው የፖለቲካ ስርዓት ስንናገር በዚሁ ሂደት
ውስጥ ከካፒታሊስት ስርዓት መቀረጽ ጋር አብሮ ስለተከሰተው
የሠራተኛ መደብ ዕድገትና ትግል ካላነሳን ስለቡርዧዋው የፖለቲካ
ስርዓት የምናደርገው ትንታኔ የተሟላ ነው ለማለት አንችልም ።

በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ ሠራተኞች ከቡርዧዋው መደብ
ይደርስባቸው ከነበረው የኢኮኖሚ ጭቆና ለመከላከል በተለያዩ
የሞያና የሠራተኛ ማህበራት በመደራጀት ጥቅማቸውን ለማስከበር
ከፍተኛ ትግል ሲያካሂዱ ቆይተዋል ። በዚህም ረገድ በየአገሮቻ
ቸው የሚገኙ የቡርዧዋ መንግሥታት አንዳንድ ለውጦችን እንዲያ
ደርጉ ሊያስገድዷቸው ችለዋል ። ለምሣሌ አነስተኛ የደመወዝ
ጭማሪ ፣ የስምንት ሰዓት ሥራ ወዘተ... መጥቀስ ይቻላል ።
በዚህ ሂደት ውስጥ የሠራተኛው መደብ አባላት የድርጅትን አስፈ
ላጊነትና ጠቃሚታ ከተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው ለመረዳት ከመቻ
ላቸውም ሌላ መላው ሠራተኛ በአንድነት ሆኖ ካልተባበረና በመደብ
ጥላቻ ካልተነሣ በስተቀር በየፋብሪካው የሚገኙ ሠራተኞች በተ
ጥል የሚያካሂዱት ትግል ፍሬያማ ሊሆን እንደማይችል ሊገነዘቡ
ዋል ። በተጨማሪም የሠራተኛው መደብ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች
ሩ የሚችሉት ሠራተኛው ከቀን ተቀን የኢኮኖሚ ጥያቄዎች
የፖለቲካ ጥያቄዎችንም በማንሳት ለአርነቱ ሲታገል መሆ
ነዘቡ በቅተዋል ፣ በዚሁ ረገድ የቀደሞ የቡርዧዋ ፈላ
ተያዮቶችና ያቀረቧቸው የመፍትሄ ሃሣቦች ለሠራተኛው
ድጋፍ የሰጠ መሆኑ ቢታወቅም በተለይ የሠራተኛው

መደብ የራሱን ርዕዮተዓለም ይዞ የፖለቲካ ስልጣኑን በእጁ ለማ ድረግ ይቻል ዘንድ አባት አብዮታዊያን ማርክስና ኤንግልስ ያበ ረከቱት አስተዋጽኦ በሠርቶ አደሩ መደብ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትግል ውስጥ ልዩ ስፍራ የሚሰጠው ነው ። በግብታዊ ንቃተ-ኅሊና ላይ የተመሠረተው የሠራተኛው መደብ ትግል በመደባዊ ንቃተ-ኅሊና ላይ ተመስርቶ ሠርቶ አደሩ የራሱን ርዕዮተዓለም በመጨበጥ የቡ ርዧዋውን መደብ የፖለቲካ ስርዓት ገርስሶ ጥሉ ለአዲስ ሶሻሊስት ሕብረተሰብ ግምባታ እንዲነሣሣ በማድረግ ረገድ ማርክስና ኤንግ ልስ በግልም ሆነ በጋራ ያበረከቱት ድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ አስተዋጽኦ በታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ይዞ የሚገኝ ነው ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የቡርዧዋውን የፖለቲካ ስርዓት በማጥቆር ረገድ የቡርዧዋ መንግሥታት እንደዚሁም የሠራተኛው መደብ የሞያና የሠራተኛ ማህበራት በስርዓቱ ውስጥ የነበራቸው ሚና ግልጽ ይመስለናል ። በተጨማሪም ከቡርዧዋው የፖለቲካ ስር ዓት መመስረት አኳያ የቡርዧዋው የሕግ ስርዓት መዳበር ፣ የቡ ርዧና ሕብረተሰብ የፖለቲካ ባህል መስፋፋትና የቡርዧዋው የፖለ ቲካ ርዕዮተዓለም መስፋፋት ለፖለቲካ ስርዓቱ መጠናከር አስተ ዋጽኦ ማድረጉን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ።

የፖለቲካ ስርዓት በሙሉ መልኩ የተከሰተው በካፒታሊ ስቱ ስርዓተ ማህበር ውስጥ ነው ሲባል የፖለቲካ ስርዓት ጽንሰ ሀሳብም ሆነ አመጣጥ ምን ጊዜም ቢሆን ከካፒታሊስቱ ስርዓት ጋር ብቻ ይያያዛል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ተገቢ ይመስለ ናል ። በዓለም ላይ የመጀመሪያው ሶሻሊስት መንግሥት እ.ኤ.አ በ1917 በሩሲያ ምድር ከተመሰረተ በኋላ የካፒታሊስቱ የፖለ ቲካ ስርዓት ብቸኛው የፖለቲካ ስርዓት መሆኑ ቀርቶ አዲስ ሶሻ ሊስት የፖለቲካ ስርዓት ለመሰረት ችሏል ። የዚህ አዲሱና መሠረ ታዊ ዓላማ የቡርዧውን የፖለቲካ ስርዓት ከሶሻሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ጋር አነፃፀሮ መተንተን ባይሆንም በተለይ በዘመናችን በሁለቱ ስርዓቶች መካከል የሚካሄደው ትግል በዓለም የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ያስከተለውን ለውጥ ከመገንዘቡ አኳያ የሶሻሊስት ስርዓት መመስረትና በተለያዩ የአውሮፓና የእስያ ሀገሮች ውስጥ

የሶሻሊስት የፖለቲካ ስርዓት መመስረትና መጠናከር ለዓለም ታሪክ ዕድገት ለዱ መልክ ሊሰጠው መቻሉን ለንረዳ እንችላለን።

እስካሁን ድረስ ስለ ፖለቲካ ስርዓት ምንነትና አመጣጥ አጠር ባለ መንገድ ለመመልከት ሞከረናል ። አሁን ደግሞ ስለ ፖለቲካ ስርዓት ምንነት በበለጠ ለመረዳት እንድንችል ስለ አካላቱ ምንነት አንዳንድ መሠረታዊ ሃሣቦችን በማንሳት ውይይታችንን እንቀጥል ።

4. የፖለቲካ ስርዓት አካላት

የፖለቲካ ስርዓት ውስጣዊ መያያዝና ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ካላቸው አራት መሠረታዊ አካላትን የያዘ ስርዓት ነው ።[10] እነዚህም ፦

1ኛ. የፖለቲካ ስርዓት ድርጅታዊ አካላት ማለትም መንግሥት፣ የፖለቲካ ፓርቲያች ፣ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ለምሣሌ የወያና የሠራተኛ ማህበራት ወዘተ...

2ኛ. የሕብረተሰቡ የምግባረ ሰብዕ ደንቦችና ድንጋጌያች ማስከበሪያ ስልቶችና ተቋሞች ማለትም ሕግ ፣ የፖለቲካ ባህልና የፖለቲካ የምግባር መመሪያዎች ፣ የሕብረተሰብ የሞራሊቲ ፋይዳዎችና ልምዶች ፣

3ኛ. የፖለቲካ ስርዓቱ አሰራር፣ ማለትም በኢኮኖሚና በፖለቲካ የበላይነት ያለው መደብ መንግሥት የሚከተሳቸው የፖለቲካ ስራዎች የአፈጻጸም ስልቶችና ዘዴዎች ፣

4ኛ. የፖለቲካ ስርዓቱ ርዕዮተዓለማዊ ዘርፎች ማለትም የፖለቲካዊ ርዕዮተዓለም መመሪያዎችና የስርዓቱ ርዕዮተዓለማዊ መሠረት የሆኑ ንድፈ ሃሣባዊ አቋሞችና ትንታኔዎች ና ቸው።

በተለምዶ አቀራረብ በዘውን ጊዜ የፖለቲካ ስርዓት አካላት የሚባሉት ፓርቲ መንግሥትና ሕዝባዊያን ድርጅቶች ብቻ ነው። እነዚህ ተቋሞች በእርግጥ የፖለቲካ ስርዓት አካላት መሆና ቸው

ባይካዱም የማናቸውም የፖለቲካ ስርዓት አካላት እነዚህ ሶስቱ ብቻ ናቸው ማለት ግን ትክክል አይደለም ፡፡ ሶስቱም በፖለቲካ ስልጣን ተግባራዊነትና እንቅስቃሴ ውስጥ በተለይም ከፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ አንፃር የሚጫወቱት ሚና ወሳኝ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም የፖለቲካ ስርዓት የሚያቅፋቸው አካላት ግን የስርዓቱን የሕግ ስርዓትና ርዕዮተዓለማዊ ዘርፎችንም የሚያቅፍ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልገናል ፡፡

በእርግጥ ሕግ የማውጣት ተግባርም ሆነ ርዕዮተዓለምን በማሰራጨት ረገድ የመንግሥትና የፖለቲካ ፓርቲ/ፓርቲያቸ/ ሚና የታወቀ ቢሆንም የአንዱ ሀገር የሕግ አወጣጥና ዕድገት ራሱን የቻለ የእንቅስቃሴ ዘርፍ ሲሆን በዚህም የሕግ ሥርዓት አወቃቀርና አፈጻጸም ረገድ የሌሎቹ የፖለቲካ ስርዓቱ አካላት ተካትተው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለጽ መሆኑ በቂ ግንዛቤ ማግኘት እንዳለበት እንገምታለን ፡፡ በርዕዮተዓለም ስርጭትም ሆነ ሕግ በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የመንግሥት ፣ የፖለቲካ ፓርቲ/ፓርቲያቸ/ እንደዚሁም የሕዝባዊያን ድርጅቶች ሚና /በተለይ በሶሻሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ/ ሰፊ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም የፖለቲካ ስርዓት ሲባል በስርዓቱ ውስጥ የሚገኙትን የፖለቲካ ተቋሞችን ፣ የስርዓቱን የሕግ ስርዓትና እንደዚሁም የርዕዮተዓለማዊ ንቃተኅሊና ዘርፍን የሚያካትት መሆኑን ማጤን ይገባናል ፡፡

ከላይ ባጭሩ የጠቃቀስናቸው የፖለቲካ ስርዓት አካላትን ስንመለከት በፖለቲካ ስርዓቱ እንቅስቃሴና ዕድገት ውስጥ የያንዳንዱ አካል ሚና አንዱ ካንዱ የተለየ ቢሆንም ለፖለቲካ ስርዓቱ ኅልውናና ዕድገት ግን የያንዳንዱ አካል ተግባር ከሌላው ጋር መያያዝና መተካሰር ለፖለቲካ ስርዓቱ ኅልውናና ዕድገት አስፈላጊ መሆኑን እንገነዘባለን ፡፡ በሌላ በኩል ግን ማናቸውም የፖለቲካ ስርዓት በአንዱ በተወሰነ የምርት ግንኙነት ዓይነት ወይንም በተወሰነ የኢኮኖሚ መሠረት ዓይነት ላይ የሚዋቀር እንደመሆኑ በያንዳንዱ የፖለቲካ ስርዓት አካላት መካከል የሚኖረው ውስጣዊ

ግንኙነት መጠናከር ወይንም መላላት ፣ የግንኙነቱ ዕድገት አቅ
ጣጫና ደረጃ እንደዚሁም በአካላቱ መካከል የሚኖረው የግንኙነት
ቅደም ተከተል እንደየፖለቲካ ስርዓቱ ዓይነት ይለያያል ።

ለምሳሌ በቡርዧዋው የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ የፖለቲካ ስር
ዓቱ ዋና ዋና ተግባሮች በአብዛኛው የሚከናወኑት በቡርዧዋው መን
ግሥትና በቡርዧዋው መንግሥት የስልጣን አካላትና የመንግሥት መዘ
ውር አማካይነት ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች በፈረቃ ስልጣን በሚይ
ዙበት ሁኔታ ውስጥ የፓርቲ አመራር ተከታታይነት ባለው መንገድ
የማይከናወን ከመሆኑም በላይ እነዚህ ፓርቲዎች /ለምሳሌ ሶሻል
ዲሞክራቲክ ፣ ወግ አጥባቂ ፣ የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ ፣
ሶሺያሊስት ፓርቲ ወዘተ/ ከሰራተኛና የሙያ ማህበራት ጋር ያላ
ቸው ግንኙነት እንደዚሁም ከመንግሥት ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት
በካፒታሊስቱ ስርዓት ውስጥ ከሚታየው ውስብስብ ርዕዮተዓለማዊ ፣
ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትግል ሂደት ውስጥ የሚከናወን ነው ።
ለምሳሌ የሙያ ማህበራት ወይንም የሠራተኛ ማህበራት ከመንግሥት
ጋር ያላቸው ግንኙነት በአብዛኛው እነዚህ ማህበራት ጥቅማቸውን
ለማስከበር ከሚያደርጉት መራራ ትግል ጋር የተያያዘ ተፃራሪ ግን
ኙነት ነው ። መንግሥትም ከተለያዩ ፓርቲዎች ጋር የሚያደርገው
መደበኛ ወይንም መደበኛ ያልሆነ ግንኙነት ከላይ ከተጠቀሰው
ሁኔታ ውጪ ሊሆን አይችልም ።

በሶሻሊስት የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ የምንመለከተው ሁኔታ
ከዚህ የተለየ ነው ። የሶሻሊስት የፖለቲካ ስርዓት በሶሺያሊስት
የምርት ግንኙነት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ የኢኮኖሚ ዕድገት፣
አደረጃጀትና አሰራር መሠረታዊ ዓላማ የሰፊውን ሕዝብ ቁሳዊ ፍላ
ጎት ማሟላት ሲሆን በስርዓቱ አካላት መካከል የተግባር ፣ የዓላ
ማና የርዕዮተ ዓለም አንድነት አለ ። ከቡርዧዋው የፖለቲካ ስር
ዓት በተለየ መልኩ በሶሺያሊስቱ ስርዓት ውስጥ የፖለቲካ ስርዓቱ
መሪ ኃይል የሠርቶ አደሩ ፓርቲ ሲሆን የመሪነት ሚናውም የሚገለ
ጸው በርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አመራር ሲቧነው ብቻ ሳይሆን
በፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት ለማስተባ
በርና ሁሉም በጋራ ለሰፊው ሕዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች

መሟላት አብረው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግም ጭምር ነው ::

ስለ ፖለቲካ ስርዓት አካላት ሲነሣ አንድ በቂ ግንዛቤ ሊያገኙ የሚገባው ጉዳይ አለ :: ማና ቸውም የፖለቲካ ስርዓት ምን ነት ወይንም ባህሪይ መታየት የሚገባው የያንዳንዱ የፖለቲካ ስር ዓቱ ባህሪይ ገርድፍ ድምር ሆኖ አይደለም :: የፖለቲካ ስርዓቱ አካላት ተገባሮች ድምር ወይንም የያንዳንዱ የፖለቲካ ስርዓቱ አካል ባህሪይ ድምር በቀጥታ የፖለቲካ ስርዓቱን አጠቃላይ ባህ ሪይ አያመለክትም :: የፖለቲካ ስርዓቱ ምንነት ባህሪይ በመሠረቱ የሚገለጸው በአካላት መካከል በሚፈጠረው ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ቢሆንም ስር ዓቱ ግን በራሱ የሚፈጠረው ባህርይ ካዋቀሩት አካላት ባህሪይ የተ ለየ ነው ::

በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ፖለቲካ ስርዓት አካላት ስንና ገር ቀደም ሲል ስለፖለቲካ ስርዓት ምንነት ስናጠና ያነሳነውን አንድ መሠረታዊ ነጥብ ማስታወስ ይገባናል :: የፖለቲካ ስርዓቱ አካላት ከፖለቲካ ስርዓቱ አኳያ ሲታዩ የአንድ ስርዓት አካላት መሆናቸው የታወቀ ቢሆንም ለምርምር ሲባል ለየብቻ ከተወሰዱ ግን እያንዳንዱን አካል እንደ አንድ ስርዓት ማየት የሚቻል መሆኑን ነው :: ለምሣሌ መንግሥትን የወሰድን እንደሆነ እንደ አንድ ስርዓት ሲታይ በውስጡ የአስተዳደር ፣ የስልጣን ፣ ወዘተ... አካላት ያሉት መሆኑን እንገነዘባለን :: በዚህ ትምህርት መጀመ ሪያ አካባቢ በስርዓትና በስርዓቱ አካላት መካከል ያለው ግንኙ ነት ወይንም ቁንጅት አንፃራዊ ነው የተባለውም ለዚህ ነው ::

ስለ ፖለቲካ ስርዓት አካላት ምንነትና ግንኙነት ስናነሣ አንድ መገንዘብ ያለብን ጉዳይ አለ :: እያንዳንዱ የፖለቲካ ስር ዓቱ አካል በስርዓቱ ውስጥ ከታቀፉት ሌሎች አካላት ጋር ግንኙ ነት የማድረጉን ያህል ከሌሎች ከፖለቲካ ስርዓቱ ዉጪ ካሉት የማ ህበራዊ ስርዓት አካላት ጋር ደግሞ ከፖለቲካ ስርዓቱ አንፃር ሲታይ ዉጪያዊ የሆነ ግንኙነት የሚያደርግ መሆኑን ነው :: ለም ሣሌ ፖለቲካዊ ንቃተኅሊናን የወሰድን እንደሆነ ከርዕዮተዓለማዊ ንቃተኅሊናና የመደብ ጥቅምን ከመገንዘብና መደባዊ ንቃተኅሊናን

ከመላበስ ጋር የተያያዘ ነው ። ይሁን እንጂ ባንድ ጐኑ ደግሞ ከሕብረተሰቡ የመንፈሳዊ ባህል ዕድገትና ታሪክ ፣ እንደዚሁም የሕብረተሰቡ አባላት በአጠቃላይ በቀን ተቀን እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ከሚያጋጥሟቸው ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በገብታዊነት በሚያውቋቸው ወይንም በሚገነዘቧቸው ሰፊ ነገሮች ላይም ጭምር የተመሠረተ ነው ። አልፎ ተርፎም የፖለቲካ ስርዓቱ ራሱ ኅልውናውን የሚያገኘው በመሠረቱ በአካላቱ መካከል ለሚፈጠረው ግንኙነትና መተሳሰር ቢሆንም ከሌሎች ከስርዓቱ ውጪ ካሉት ሌሎች ስርዓቶችና ከስርዓቶቹ አካላት ጋር የሚኖረውም <u>ውጪያዊ ግንኙነት</u> እንደሚኖር መገንዘብ ያስፈልገናል ። ለምሣሌ በአንድ ማኅበራዊ ስርዓት ውስጥ ገኖ የሚታየው የፖለቲካ ስርዓት ከስርዓቱ ውጪ ከሆነው ሌላ ስርዓት /ለምሣሌ የባህልና ወግ ስርዓት/ ጋር ያለው ነባራዊ ግንኙነት በስርዓቱ ምንነትና ተግባር ላይ ተፅዕኖ የማድረግ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ማጤን ይገባል ።

ይህ ስለተባለ ደግሞ የፖለቲካ ስርዓት እድገት በሙሉ መልኩ የሚወሰነው ከስርዓቱ ውጪ ካሉ ሌሎች የማህበራዊ ስርዓት አካላት ጋር ባለው ግንኙነት ብቻ ነው ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ይኖርብናል ። ውጪያዊ ክስተቶች በአንድ ነገር ወይንም ክስተት ዕድገት ላይ የማዘግየት ወይንም የማፋጠን ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ ። እንጂ በነገሩ ወይንም ከክስተቱ ዕድገት ላይ የፍጻሜ ወሳኝነት ሚና ሊኖራቸው አይችልም ።

እስካሁን ድረስ የፖለቲካ ስርዓትን ምንነት ፣ አመጣጥና አካላቶቹን አጠር ባለ መልክ በመመልከት አንዳንድ መሠረታዊ ሐሳቦችን ለማንሳት ሞክረናል ፣ ስለ ፖለቲካ ስርዓት የምናደርገውን ትንተና በመጠኑም ቢሆን በማስፋት ስለ ባህሪያቶቹ አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦችን በማንሳት እንወያይ ።

5. <u>የፖለቲካ ስርዓት መሠረታዊ ባህሪያት ወይም ጠባዮች</u>

ቀደም ሲል ስለ ፖለቲካ ስርዓት ምንነት ስንነጋገር የፖለቲካ ስርዓትን ከሌሎቹ የማህበራዊ ስርዓት ዘርፎች ሁሉ ዓይነተኛ

የሚያደርገው ከሌሎች የማህበራዊ ስርዓት አካላት ሁሉ የበላይ መሆኑና በሕብረተሰብ ውስጥ ላዕላይ ስልጣን ያለውና መመሪያዎቹ ደንቦቹ ሁሉ በሕብረተሰቡ ዘንድ እንደዚሁም በስርዓቱ አካላትም ዘንድ የግዴታ ተፈጻሚ የሚሆኑ መሆና ቸውን ባጭሩ ጠቅሰን ነበር፡፡ የፖለቲካ ስርዓት ከዚህ ከተጠቀሰው መሠረታዊ ባህሪዩ ሌላ ሌሎች ባህሪያት አሉት ፡፡ እስቲ እነዚህን ባህሪያት ባጭሩ ለመቃኘት እንሞክር ፡፡

የፖለቲካ ስርዓት በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ቀንበር ውስጥ የሚይዘው ስፍራ የት ነው ? የፖለቲካ ስርዓት የላዕላይ መዋቅር አካል ነው ፡፡ እንደላዕላይ መዋቅር አካልነቱ ደግሞ የተመሠረተ በትን ወይንም ሕልውና የሰጠውን የኢኮኖሚ መሠረት ያንፀባርቃል ሕልውና ለሰጠው መደብ ያገለግላል ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ማና ቸውም የፖለቲካ ስርዓት የተመሠረ ተበትን ኢኮኖሚ መሠረት ያንፀባርቃል ቢባልም ባንድ አንፃር የፖለቲካ ስርዓት ከተመሠረተበት የኢኮኖሚ መሠረት አንፃራዊ ነፃነት ያለው መሆኑን እንገነዘባለን ፡፡

ይህ ለምን ይሆናል ? እንዴትስ ይገለጻል ?

በመሠረቱ የሕብረተሰብን የኢኮኖሚ መሠረት ዕድገት በሚገዙ ሕገጋትና ህገጋት ያላዕላዊ መዋቅሩ አካል የሆነውን የፖለቲካ ሥርዓትን በሚገዙ መካከል ልዩነት አለ ፡፡ በሌላ አንፃር ደግሞ በሕብረተሰብ የኢኮኖሚ ዕድገትና በፖለቲካ ስርዓት ውስጥ የሚታዩትን ለውጦች ስንመለከት የኢኮኖሚ ዕድገት ከፖለቲካ ስርዓት ዕድገት አንፃር ሲታይ በዝግታነት የሚከናወን ሲሆን ፤ በፖለቲካ ስርዓት የሚታዩ ለውጦች ግን ፈጣንና ታዳጊ ና ቸው ፡፡

የፖለቲካ ስርዓት ባህሪይ ከሚገለጽባቸው መስኮች አንዱ በማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ ሌሎች የሥርዓቱ አካላት ከፖለቲካ ሥርዓት ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት በተወሰኑ ፖለቲካዊ ወይንም ሕጋዊ የግንኙነት ሥርዓት ላይ መመሥረቱ መሆኑ ነው ፡፡[11] ለምሳሌ ልዩ ልዩዎቹ የማኅበራዊ ሥርዓት አካላት ከፖለቲካ ጋር ቲያቸ

ወይንም ከመንግሥት ወይንም ከሕዝባዊያን ድርጅቶች ጋር የሚያደርጉቸው ግንኙነቶች በተወሰኑ የሕግ ሥርዓቶች ወይንም ድንጋጌዎች ወይንም የፖለቲካ መርሆዎች ላይ የሚመሠረቱ ናቸው ።

በተጨማሪም ከሌሎች የማኅበራዊ ሥርዓት አካላት ሁሉ ይልቅ የፖለቲካ ሥርዓት የላቀ ሥልጣንና ኃይልን የሚያንቀሳቅስ በመሆኑ የተነሣ በተቀረት የማኅበራዊ ኑሮ ዘርፎች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ሌሎች የማኅበራዊ ሥርዓት አካላት በሕብረተሰብ ኑሮ ከሚያደርሱት ተፅዕኖ ይበልጥ ጥልቀትና ስፋት ያለው ነው ።[12]

ከላይ የጠቀስናቸው የፖለቲካ ሥርዓት መሠረታዊ ባህርያት የማናቸውም የፖለቲካ ሥርዓት መሠረታዊ ባህርያትን የሚያመለክቱ እንጂ አንዱን ዓይነት የፖለቲካ ሥርዓት ብቻ የሚገልጹ አይደሉም።

የማናቸውም የፖለቲካ ሥርዓት ባህርይ ከላይ ባጭሩ እንደተገለፀው የፖለቲካ ሥርዓቱ ከሌሎች የማኅበራዊ ሥርዓት አካላት ጋር በሚኖረው የግንኙነት ዓይነትና ደረጃ ይገለጻል ። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ የፖለቲካ ሥርዓት ዓይነት የሚኖረው መሠረታዊ ባህርይ የፖለቲካ ሥርዓቱ እንደተመሠረተበት የኢኮኖሚ መሠረት ወይንም የኢኮኖሚ ግንኙነት ዓይነት ሊለያይ እንደሚችል መገንዘብ ጠቃሚ ይመስለናል ። ለምሳሌ የቡርዧው የፖለቲካ ሥርዓት ባህርይ የተለየ ነው ። የፖለቲካ ሥርዓት በአጠቃላይ የሚኖረው መሠረታዊ ባሕሪ አንድ ወጥ ቢሆንም እያንዳንዱ የፖለቲካ ሥርዓት ዓይነት አንዱ ከአንዱ የሚለይበት የራሱ የሆነ መለያ ባህርያት ይኖሩታል ።

እስካሁን ድረስ የፖለቲካ ስርዓትን መሠረታዊ ባህርያት አጠር ባለ መንገድ ለመተንተን ባደረገነው ሙከራ አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችን ለማንሳት እንደቻለን እንገምታለን ። አሁንም ስለ ፖለቲካ ስርዓት ምንነት የምናካሂደውን ውይይት ሰፋ በማድረግ የፖለቲካ ስርዓት መሠረታዊ ተግባሮችን እንመለከታለን ።

6.፡ <u>የፖለቲካ ስርዓት ተግባሮች</u>

የፖለቲካ ስርዓት መሠረታዊ ተግባሮች ከፖለቲካ ስርዓት አመጣጥ ምንነትና አካላት ጋር የተያያዙ ተግባሮች ናቸው ። እነዚህ መሠረታዊ ተግባሮች ምንድንና ቸው ? የፖለቲካ ስርዓትን መሠረታዊ ተግባሮች በአምስት ልዩ ልዩ ደረጃዎች ከፋፍለን ማየት እንችላለን ።

የፖለቲካ ስርዓት አንዱ ተግባር <u>የፖለቲካ ስርዓቱ ከተመሠረተበት ዓላማና ከሚያከናውናቸው ተግባሮች አኳያ የሕብረተሰቡን አጠቃላይ ዓላማና ተግባር መወሰን ነው ።</u>[13] ይህ አባባል ምንን ያመለክታል ? ለምሳሌ የሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓትን መሠረታዊ ዓላማ እንመልከት ። የሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት መሠረታዊ ዓላማ የሰፊውን ሕዝብ ማቴሪያላዊና መንፈሳዊ ፍላጐት በማሟላት የተሟላ ስብዕናና ሁለገብ ብቃት ወይንም ችሎታ ባላቸው ዜጐች የተገነባን ሶሺያሊስት ሕብረተሰብ መፍጠርና ማጠናከር ነው ፤ እንግዲህ ሶሺያሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የሕብረተሰቡን አጠቃላይ ዓላማና ተግባሮችን ከዚሁ አጠቃላይ ዓላማ መሟላት ጋር በተገናዘበ መልኩ ይወስናል ማለት ነው ። በመሠረቱ ይህ ደግሞ ተግባራዊ የሚሆነው የፖለቲካ ስርዓቱ መሪ ኃይል የሆነው የሠርቶ አደሩ ፓርቲ ለሕብረተሰቡ በሚሰጠው ድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ አመራርና እንደዚሁም በመንግሥት በኩል በሚወጡ ልዩ ልዩ አዋጆች ፣ ድንጋጌዎች ፣ የሕዝብ ማስታወቂያዎች ወዘተ አማካይነት ነው ።

የፖለቲካ ስርዓት ተግባር ከላይ በተጠቀሰው ብቻ የሚወሰን አይደለም ። ይልቁንም የፖለቲካ ስርዓት ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎችና ተግባሮችን ለማከናወን የሚያስችሉትን <u>የሀገሪቱን ጥሬ ሀብትና ልዩ ልዩ ማቴሪያላዊ ሀብቶችን የማንቀሳቀስ የመጠበቅ ተግባር ላይ የማዋልና አጠቃቀማቸውንም በማመልከት ልዩ ልዩ ሕጐችን ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ያወጣል ።</u>

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁለት የፖለቲካ ስርዓት ተግባሮች የፖለቲካ ስርዓቱ ዋነኛ ተግባሮች የሚባሉ ናቸው ። እንዲያም

ሲባል የፖለቲካ ስርዓት ተግባር በነዚህ ሁለት መሠረታዊ ተግባ ሮች ብቻ ይወሰናል ማለት አይደለም ።

ሌላው የፖለቲካ ስርዓት ዓይነተኛ ተግባር በፖለቲካ ስርዓቱ አካላት መካከል የሚኖሩ ግንኙነቶች የተወሰኑ ሕጎችን ፣ደንቦችንና የስነ ሥርዓት ወይንም የአሰራር መመሪያዎችን ተከትለው የሚካናወኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ስርዓቱ የዜጎችን መብትና ግዴታዎችን በሕግ የመደንገግና ተፈጻሚነታቸውንም የማረጋገጥ ተግባር ይፈጽማል።

ለምሣሌ የሶሺያሊስቱን የፖለቲካ ስርዓት ብንወስድ የፓርቲው የፖለቲካ ስርዓቱ መሪ ኃይልነት በሕግ የሚገለጸው በሶሺያሊስቱ ሕገ መንግሥት አማካይነት ሲሆን ፓርቲው ደግሞ በሶሺያሊስቱ መንግሥት የሕግ ስርዓት ደንቦች ውስጥም ጥምር ተግባሮችን የሚያከናውን መሆኑን እንገነዘባለን ፣ ሌሎች የፖለቲካ ስርዓቱ አካላት ከመንግሥትም ሆነ ከፓርቲው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በሶሺያሊስቱ ሕገ መንግሥት በሚደነገገው መሠረት ነው ። ከዚህም በላይ በሕግና ፍትህ አስተዳደርና አፈጻጸም ሂደት ውስጥ የሶሺያሊስት ሕጋዊነት መሠረተ ሃሣቦች ተግባራዊ የሚሆኑበትና በመንግሥት ስልጣን አመሰራረትና አሰራር ውስጥ የሰፊው ሕዝብ የነቃ ተሳትፎ በሕግ በሚደነገገው መንገድ የሚፈጸም መሆኑ አንዱ የሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት ሕጋዊ እንቅስቃሴ መገለጫ ነው ።

ሌላው የፖለቲካ ስርዓት ተግባር ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በሕብረተሰቡ ስም የበላይ ሉአላዊ ስልጣን መያዝና በአስከናዊ በፖለቲካ የበላይነት ያለውን መደብ ጥቅም ማስከበር ነው ። በፖለቲካ ስርዓቱ በአጠቃላይ የሚደነገጋቸው ሕጎችና የሚያወጣቸው ደንቦች በሌሎቹ የፖለቲካ ስርዓቱ አካላት ዘንድ ያላንዳች ማወላወል ተግባራዊ ይሆናሉ ።

የፖለቲካ ስርዓቱ መሠረታዊ ተግባሮች በአጠቃላይ ሲታዩ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባሮች የሚያቅፉ ሲሆን እያንዳንዱ የፖለቲካ ስርዓቱ አካል ግን የፖለቲካ ስርዓቱን መሠረታዊ ተግባሮች

በማከናወን ረገድ የሚኖረው ተሳትፎ ግን በደረጃም ሆነ በስፋቱ
የተለያየ ነው ። የአንዳንዶቹ የፖለቲካ ስርዓት አካላት ተግባ
ሮች በአብዛኛው በአንድ አቅጣጫ የሚያዘነብሉ ናቸው ለምሳሌ
የፖለቲካ ፓርቲዎች ተግባር በአብዛኛው ፖለቲካዊ ነው።[14] ሌሎች
ደግሞ የተለያዩ ተግባሮችን ይፈጽማሉ ። ለምሳሌ የሠራተኛ ማህበ
ራት ከፖለቲካ ተግባሮቻቸው በተጨማሪ የሠርቶ አደሩን ኑሮ ለማ
ሻሻል ይቻል ዘንድ አንዳንድ ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊና ማህበራዊ
ተግባሮችንም ያከናውናሉ ።

ይህ ስለ ተባለ ደግሞ የፖለቲካ ስርዓት መሠረታዊ ተግባ
ሮች የስርዓቱ አካላት ተግባሮች ድምር ነው ማለት አይቻልም ።
የዚህ ማረጋገጫ ምንድን ነው ? በመሠረቱ የፖለቲካ ስርዓት
የአካላቱ ገርድፍ ድምር ውጤት ሳይሆን በአካላቱ መካከል ከሚኖ
ረው ውስጣዊ መያያዝና መተሳሰር የሚመነጭ መሆኑ ግልጽ ሊሆን
ይገባል ፣ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የፖለቲካ ስርዓቱ የሚኖ
ረው ባህሪይ የያንዳንዱ የፖለቲካ ስርዓቱ አካላት ባህሪያት
ድምር ውጤት አይደለም ። ስለሆነም የፖለቲካ ስርዓቱ አጠቃላይ
ባህሪይ እያንዳንዱ የስርዓቱ አካል ከሚኖረው ባህሪይ የተለየ
ነው ። ከዚህም የተነሳ የፖለቲካ ስርዓቱ አጠቃላይ ተግባር የያ
ንዳንዱ የስርዓቱ አካላት ዝርዝር ተግባሮች ድምር ሊሆን አይች
ልም ማለት ነው ።

እስካሁን ድረስ የፖለቲካ ስርዓትን መሠረታዊ ተግባሮች
ባጭሩ ተመለከትናል ። እዚህ ላይ አንድ መገንዘብ የሚገባን
ጉዳይ አለ ። እንደ ማንኛውም ማህበራዊ ክስተት ወይንም ተቋም
የፖለቲካ ስርዓት የማያድግ የማይለወጥ ወይንም ቋሚ ሳይሆን
ይልቁንም ታዳጊ ፣ ተሸጋጋሪ ተንቀሳቃሽ ነው ። እያንዳንዱ
የፖለቲካ ስርዓት ከተመሠረተበት የኢኮኖሚ መሠረት አኳያ አንዳ
ንድ ቋሚ ባህሪያት ያሉትና አንዳንድ መሠረታዊ ተግባሮችን የሚ
ያከናውኑ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በያንዳንዱ የፖለቲካ ስርዓት ተግ
ባር ስፋትና ጥልቀት ከፖለቲካ ስርዓቱ ውስጣዊ ዕድገት ጋር
አብሮ የሚንቀሳቀስና ስፋትና ጥልቀት እያገኘ የሚሄድ ይሆናል ።

ለምሳሌ የሶሺያሊስቱን የፖለቲካ ስርዓት አሁንም እንመልከት ። ሶሺያሊዝም የኮሚኒስት ስርዓተ ማህበር አንዱ ደረጃ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም በራሱ ግን የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ መገንዘብ እንችላለን ። ለምሳሌ የሽግግር ወቅት ፣ የግምባታ ወቅት ፣ የዳበረ ሶሺያሊስት የዕድገት ደረጃ እየተባለ ይከፋፈላል ። በነዚህ የሶሺያሊስቱ ስርዓት ውስጥ በሚታዩት የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ የሶሺያሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት የሚያከናውናቸው ተግባሮች በዚሁ መልክ ስፋትና ጥልቀት እያገኙ እንደሚሄዱ መገንዘብ አያዳግትም ።

የፖለቲካ ስርዓት አበይ ተግባሮች ከላይ ባጭሩ የጠቃቀስናቸው ሲሆኑ ለእነዚህ ተግባሮች መሠረታዊ ይዘት የሚወስንባቸውን አበይ ነገሮች ባጭሩ እንመልከት ።

በፖለቲካ ስርዓቱ ውስጥ ገኖ የሚታየው ርዕዮተዓለም በስርዓቱ ውስጥ በኢኮኖሚ በፖለቲካ የበላይነት ባለው መደብ ጥቅም ይወሰናል ። በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ስርዓትን ተግባር በመወሰን ረገድ /በቀጥታ ባይሆንም በተዘዋዋሪ/ ሕብረተሰቡ የደረሰበት የባህል ዕድገት ደረጃ የፖለቲካ ባህሉ የዕድገት ደረጃ ፣ ልዩ ታሪካዊ ሁኔታዎችና የፖለቲካ ንቃተኅሊና የዕድገት ደረጃ የተወሰነ ሚና ሊኖራቸው እንደሚችል መገመት እንችላለን ። ማናቸውም የፖለቲካ ስርዓት ተግባሮችን የሚያከናውነው የቆመለትን መደብ ጥቅም ለማስጠበቅ ቢሆንም ይህንን ለማከናወን ግን ከላይ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባው የታወቀ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ የማናቸውም የፖለቲካ ስርዓት ተግባር ከአሮጌው የፖለቲካ ስርዓት የዕድገት ደረጃ አንፃር ሲታይ አዲስ ይምሰል እንጂ አዲስነቱ ግን በፍጹም መልኩ አይደለም ። ለምሳሌ የቡርዧዎውን የፖለቲካ ስርዓትና የሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓትን ተግባሮች ብናነፃፅር በቡርዧዎው የፖለቲካ ስርዓት ውስጥም ሆነ በሶሺያሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ የፖለቲካ ስርዓቱ አንዱ መሠረታዊ ተግባር የሕብረተሰቡን ዓላማና ተግባር መወሰን ነው።

በዚህ አንፃር ብቻ በሶሺያሊስቱና በቡርዧዋው የፖለቲካ ስርዓት ተግባሮች ውስጥ ተመሳሳይነት ያለ በመሆኑ የሕብረተሰቡን ዓላማና ተግባር መወሰን የሚለው ተግባር በቡርዧዋው ስርዓት ውስጥ ቡርዧዎ ጠቀም በሆነ መንገድ ተግባራዊ ሲሆን በሶሺያሊስቱ ስርዓት ውስጥ ግን የሰፊውን ሰርቶ አደር ሕዝብ ማቴሪያላዊና መንፈሳዊ ፍላጎት ከማሟላት አኳያ ተግባራዊ ይሆናል ። ይህ የፖለቲካ ስርዓትን መሠረታዊ ተግባር አስመልክቶ የተደረገ ማነፃፀር እንጂ የሁሉም የፖለቲካ ስርዓቶች ተግባሮች ይዘት አንድ ነው ማለት አይደለም ።

የፖለቲካ ስርዓት ተግባሮች ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ የእንቅስቃሴ ወይንም የክንዋኔ ዘርፎችን ሁሉ የሚያካትት ሲሆን የእያንዳንዱ የፖለቲካ ስርዓት መሠረታዊ ተግባር ይዘት ግን እንደየፖለቲካ ስርዓቱ የዕድገት ደረጃ ይለያያል ። ስለሆነም ይህንኑ በበለጠ ለማረዳት እንድንችል የፖለቲካ ስርዓትን የዕድገት ደረጃዎች ምንነት ባጭሩ እንመልከት ።

7. የፖለቲካ ስርዓት የዕድገት ደረጃዎች

የፖለቲካ ስርዓት በአንድ የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ በተሟላ መልኩ ብቅ ያለ ማህበራዊ ክስተት ሳይሆን የረጅም ዘመን የህብረተሰብ ዕድገት ውጤት ነው ። በህብረተሰብ ዕድገት ሂደት ውስጥ የተለያዩ የፖለቲካ ስርዓት የዕድገት ደረጃዎች ታይተዋል። ይህም ከባሪያ አሳዳሪ ስርዓተ ማህበር እንስቶ በዳበረ ሶሺያሊስት ኢኮኖሚ ላይ እስከተገነባው የሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት ምሥረታ የሚደርስ ነው ።

7.1 ቅድመ ካፒታሊስት የፖለቲካ ስርዓት

በቅድመ መደብ ሕብረተሰቦች ውስጥ የነበሩ ማህበራዊ ግንኙነቶች በዘር ዝምድና ላይ የተመሰረቱ ጠባብ ግንኙነቶች ነበሩ ። በወቅቱ በሕብረተሰቡ ዘንድ ገኖ ይታይ የነበረው የማህበራዊ ኑሮ ስርዓት በልማድ ደንቦች ላይ የተመሠረተ እንጂ በሕግ መልክ የተደነገገ አልነበረም ።[15] መደቦች

ከተከሰቱ በኋላ ግን በያንዳንዱ የመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ ጐላ
ብሎ የታየው የማህበራዊ ግንኙነት ዓይነት በሕብረተሰብ መደቦች
መካከል የተፈጠረው ሁለገብ ግንኙነት ነው ። ከመደቦች መከሰት
ጋር አብሮ የተከሰተው መንግሥት የተሰኘውም ማህበራዊ ተቋም ይህ
ንኑ ግንኙነት ሕጋዊና መደባዊ አድርጐታል ።

በሕብረተሰብ ዕድገት ታሪክ የተከሰተው የመጀመሪያው ዓይ
ነት መንግሥት የባሪያ አሳዳሪ ስርዓት መንግሥት ሲሆን ይህም
የመንግሥት ዓይነት የተለያዩ ቅርጾች የነበሩት ቢሆንም ዞር ዞር
በባሪያ መደብ አባላት ጉልበት ብዝበዛ ላይ የተመሠረተና በስር
ዓቱ ውስጥ ገኖ ይታይ የነበረውን የባሪያ ስርዓት ስለተ ምርት
የሚያጠናክር ነበር ። በባሪያ አሳዳሪው ስርዓት ውስጥ የነበሩት
የተለያዩ የባህልና የኃይማኖት ተቋሞች በዓላማቸውም ሆነ በአሰ
ራራቸው ከገዢው መደብ መንግሥት ጋር የተቀራረቡ ነበሩ ። የሕዝ
ቡን መንፈሳዊ ሕይወት ለባሪያ ገዢ መደቦች በሚያመች መንገድ
በመቅረጽ ረገድ የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነበር ። እነዚህ የሃይ
ማኖትና የባህል ወይንም የዘልማዱ ተቋሞች የመንግሥትን የበላይነ
ትና ሁለንተና ዊነት ይሰብኩ ነበር ። የመንግሥቱ የፖለቲካ ፖሊሲ፣
ፍላጐትና ድርጊት ሁሉ ትክክል መሆኑን ለማሳመን ይሞክሩ ነበር ።

በእርግጥ በባሪያ አሳዳሪ ስርዓት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ
ዎች ፣ የሙያ ማህበራት ዛሬ በሚታወቁበት መልክ ያልነበሩ ቢሆ
ንም የገዢውን መደብ ጥቅም የሚወክሉ የተለያዩ ማህበራዊ ተቋሞች
እንደነበሩ ግልጽ ነው ።

በፊውዳሉ ስርዓት ውስጥ የመንግሥት መሠረታዊ ተግባሮችና
ዓላማዎች በባሪያ አሳዳሪ ስርዓት ውስጥ ከነበሩት መንግሥታዊ
ተግባሮችና ዓላማዎች የሰፉ ነበር ። በፊውዳሊዝም ውስጥ በመንግ
ሥትና በኃይማኖት ተቋሞች መካከል ከፍተኛ መደጋገፍ የነበር
ሲሆን ንጉሡ ራሱ በዓምላክ ፈቃድ የነገሡ መሆኑ የሚነገርለት
ነው ። በፊውዳሊዝም ውስጥ ኃይማኖታዊ ቀኖና ዊነት የሰፈነ ስለ
ሆነ አዳዲስ ነገሮችን የማፍለቅ ፣ አዳዲስ ሃሳቦችን የማቅረብና
መንግሥትም ላይ ትችት ማቅረብ የማይቻልበት የፖለቲካ ሁኔታ

የሰፈነበት ነው ።

በፊውዳሉ ስርዓት ውስጥ በመንግሥት የሚወጡት ሕጎች በይዘታቸው የፊውዳሉን ስርዓት የሚያጠናክሩ ሲሆኑ የባህልም ሆነ የሌሎች የማህበራዊ ግንኙነቶች ዘርፎች ርዕዮተዓለማዊ መሠረት ኃይማኖት ነው ። በዚህ ስርዓት ውስጥ ሕዝቡ በመንግሥት አስተዳደርም ሆነ ስልጣን ውስጥ ምንም ተግባራዊ ተሳትፎ የሌለው ሲሆን በአንዳንድ ሁኔታዎች አነሳሽነት የሚቋቋሙት የሠራተኛና የሞያ ማህበራት እንኳን እንዳይደራጁ የማይፈቀድበት ሁኔታ ታይቷል ።

በሕብረተሰብ የፖለቲካ አደረጃጀት ሂደት ውስጥ በተለይም ተፃራሪ መደቦች በሚገኙበት ሕብረተሰብ ውስጥ የፖለቲካ ስርዓት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰው በካፒታሊስቱ ስርዓተ ማህበር ውስጥ ነው ።

7.2 የካፒታሊስቱ የፖለቲካ ሥርዓት

የካፒታሊስቱ የፖለቲካ ሥርዓት አመሠራረት በአንድ ወቅት የተከናወነ ማህበራዊ ክንዋኔ ሳይሆን የረዥም ዘመን የካፒታሊስቱ ስርዓት የዕድገት ውጤት ነው ።

በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ ቀደም ሲል የተመሠረቱት የፊውዳል መንግሥታት በተለያዩ ምክንያቶች ተንኮታኩተው ሲወድቁ በምትካቸው የቡርዧዋ መንግሥታት ተመሠረቱ ። የቡርዧው መደብ በነፃነት ፣ በእኩልነትና በወንድማማች አርማ ሥር ራሱንና ሌሎችንም የሰፊውን ሕዝብ ወገኖች /የሠራተኛውን መደብ ጭምር/ በማሰለፍ የራሱን መንግሥት ለመስርት ችሏል ። በካፒታሊስቱ ስርዓት ውስጥ የቡርዧዋው መደብ የፖለቲካ ስልጣን ከጨበጠ በኋላ በፊውዳሉ ስርዓት ውስጥ ያልተለመዱ አንዳንድ ለውጦችን አድርጓል ። ከነዚህም መካከል የምርት ኃይሎችን ማሳደግ ፣ ከቡርዧዋው መደብ ጥቅም ጋር በተያያዙ መልክም ቢሆን አንዳንድ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መስጠት፣ በመንግሥትና በቤተክህነት መካከል የነበረውን ጠበቅ ያለ ግንኙነት ማላላት ጥቂቶቹ ናቸው ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የካፒታሊስቱ ስርዓት የምርት ኃይሎች አንፃራዊ ዕድገት የታየበት በልዩ ልዩ የተፈጥሮና የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች ውስጥ ሰፊ ጥናትና ምርምር የተደረገበት ወቅት ነው ። የካፒታሊስቱ ስርዓት የምርት ግንኙነት የምርት አደረጃጀትና የሠራተኛው መደብ የኢኮኖሚ ጥቅሞችን ለማስከበር እንዲችል በልዩ ልዩ የሞያና የሠራተኛ ማህበራት ሥር ሊደራጅ የሚችልበት ቁሳዊ ሁኔታ ፈጥሮለታል ። በነዚህ ማህበራት አማካይነት የሠራተኛው መደብ ለኢኮኖሚ መብቶቹ መከበር ሰፊ ትግል አካሂዷል እነዚህ ትግሎች ግን በይዘታቸው ጠበብ ያሉና ገብቃዊ ነበሩ ።

በካፒታሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ የተቋቋሙት ማህበራዊ ተቋሞች የቡርዧዋው መንግሥትና የሠራተኛና የሞያ ማህበራት ብቻ አልነበረም ። በካፒታሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ከተመሠረቱት የፖለቲካ ተቋሞች መካከል የቡርዧዋው የፖለቲካ ፓርቲዎችም ይገኙባቸዋል ። የነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመሠራረት በቡርዧዋ መንግሥታት ውስጥ ከሚኖራቸው የፖለቲካ ሚና ጋር የተያያዘ ነው ። እነዚህ የቡርዧዋውንና የንዑስ ከበርቴውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስከበር የተመሠረቱት ፓርቲዎች /ለምሳሌ የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ፣ ሶሺያል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ፣ ወግ አጥባቂ ፓርቲዎች / በቡርዧዋ መንግሥታት ውስጥ በሚከናወኑት ምርጫዎች የመንግሥት ስልጣን ይይዛሉ ። አለፍ አለፍም የጥምር መንግሥት ይመሰርታሉ ።

በካፒታሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ የመሪነት ሚና ያለው የቡርዧዋው መንግሥት ነው ። የቡርዧዋ ፓርቲዎችም መሠረታዊ ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የሚታገሉት በዚሁ መንግሥት እየተፈራረቁ ስልጣን በመያዝ ነው ። የካፒታሊስቱ ስርዓት አብይ ዓላማ የካፒታሊስቱን የምርት ግንኙነት መጠበቅና ማጠናከር ነው ። የቡርዧዋው መንግሥት የሚያወጣቸው ሕጎችና ደንቦች፣ የሚመሰርታቸውም የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችና የመከላከያና የደህንነት ተቋሞች መሠረታዊ ዓላማ ይህንኑ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን ስርዓት ማቆየት ነው ።[16]

የካፒታሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ተግባሮችን የሚያከናውነው በውጥረትና በቀውስ ውስጥ ነው ። በፖለቲካ ስርዓቱ ውስጥ ተፃራሪና ታቃራኒ ዓላማና ፍላጎት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎችም መሰል ተቋሞች ይገኛሉ ። ይህም ሁኔታ በቡርዣዋ ፓርቲዎች መካከል በሚታዩት ፉክክሮች በሠራተኛ ማህበራት በሚካሄዱ ልዩ ልዩ የሥራ ማቆም ትግሎችና በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ በሚታዩት የስርዓት አለበኝነት የሥራ አጥነትና የፖለቲካ ቀውሶች ይገለጻሉ ።

የካፒታሊስቱ የፖለቲካ ስርዓት ርዕዮተዓለማዊ መሠረት የቡርዧዋው ርዕዮተዓለም ነው ። የቡርዧዋ መንግሥታት ይህንን ርዕዮተዓለም እንደ ሕዝብ ርዕዮተዓለም አድርገው በማቅረብ የተለያዩ የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ስልቶችን በመጠቀም በሕዝቡ ዘንድ ብሔረተኝነትና የፀረ ኮሚንስት አስተሳሰቦች እንዲሰራፉ ያደርጋሉ ። ይሁን እንጂ በነዚህ አገሮች ውስጥ የተመሠረቱት የኮሚንስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች ፣ የሠራተኛና የሌሎች ዲሞክራቲክ ኃይሎች ለሠራተኛው ጥቅም ፣ ለዓለም ሰላምና ለጦር መሣሪያ ቅነሣ የሚያደርጉት ትግል እንደቀጠለ ነው ።

እስካሁን ድረስ የቡርዧዋውን የፖለቲካ ስርዓት አመጣጥና ባህሪይ ባጭሩ ተመለከትናል ። አሁን ደግሞ የሽግግር ወቅት የፖለቲካ ስርዓት ምን እንደሚመስል አጠር ባለ መንገድ ለማየት እንሞክራለን ።

7.3 <u>የሽግግር ወቅት የፖለቲካ ስርዓት</u>

ስለ ሽግግር ወቅት የፖለቲካ ስርዓት በዝርዝር ከማንሳታችን በፊት ይህ ሽግግር ከየት ወዴት ነው የሚለውን ጥያቄ ማንሳት አለብን ። የሽግግር ወቅትን በሁለት መልክ ማየት ይቻላል እነዚህም ፦

1ኛ. ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረግ ሽግግር
2ኛ. ከቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ወደ ሶሺያሊዝም የሚደረገው ሽግግር ነው ።

ከዳበረ ወይንም በመካከለኛ ደረጃ ካደገ ካፒታሊስት የሕብረተ
ሰብ የዕድገት ደረጃ ወደ ሶሺያሊዝም በሚደረገው የሽግግር
ሂደት ውስጥ የሚመሠረተውን የፖለቲካ ስርዓት አንዳንድ ባህሪ
ያት ባጭሩ እንመለከት ። ከካፒታሊስት የሕብረተሰብ የዕድገት
ደረጃ ወደ ሶሺያሊዝም በሚደረገው ሽግግር ለሶሺያሊስት የፖለ
ቲካ ስርዓት ቁሳዊና ማቴሪያላዊ መሠረት የሚጣለው በቀድሞው
ስርዓት /ማለትም በካፒታሊስቱ ስርዓት/ ውስጥ ነው ። በተለ
ይም ለሶሺያሊስት ግምባታ አስፈላጊ የሆነው የተወሰነ የምርት
ኃይሎች ዕድገት ደረጃ በዚሁ ስርዓት ውስጥ ይመሠረታል ።
ከታሪክ ለመረዳት እንደምንችለው የሠርቶ አደሩ ፓርቲዎች ፣
የሠርቶ አደሩ ርዕዮት ዓለም ራሱ የተቀነባበረው ካፒታሊዝም
በዓለም ላይ ገኖ በታየበት ዘመን ነበር ። ይሁን እንጂ ሶሺ
ያሊስት የምርት ግንኙነትና የሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት ገን
ሊመሠረት የሚችለው የሠርቶ አደሩ መደብ የፖለቲካ ስልጣኑን
ከቡርዧዋው መደብ እጅ በመንጠቅ የሠርቶ አደሩን የበላይ ገዢ
ነት መንግሥት ሲመሰርት ነው ።

ከቀድሞ ካፒታሊስት የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ወደ ሶሺ
ያሊዝም በሚደረገው ሽግግር ውስጥ የሚመሠረተው መንግሥት የሽግ
ግር መንግሥት ነው ። የዚህም መንግሥት መሠረታዊ ተግባር ወደ
ሶሺያሊዝም ለሚደረገው ሽግግር አስፈላጊውን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖ
ሚያዊና ባህላዊ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው ። የፖለቲካ
ስርዓቱም የሽግግር የፖለቲካ ስርዓት ነው ። የዚህም ዋናው
ምክንያት የአሮጌው የፖለቲካ ስርዓት አንዳንድ አካላትና የአ
ዲሱ የፖለቲካ ስርዓት አካላት በጣምራ መገኘት ነው ። ይህንን
ሁኔታ በበለጠ ለማብራራት ባሁኑ ጊዜ በሀገራችን የሚታየውን
የፖለቲካ ስርዓትን እንደ ምሣሌ በመውሰድ እናብራራዋለን ።

ለምሣሌ ባሁኑ ጊዜ በአገራችን የሚሰራበትን የሕግ ስር
ዓት ፣ አንዳንድ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን አወቃቀር ፣
የዳኛ አካላትን አሰራርና አወቃቀር ብንመለከት ከሞላ ጎደል
አንዳንድ ለውጦች የተደረጉባቸው መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በአመዛኙ
ግን በአወቃቀርና በአሰራር ደረጃ በቀድሞው ስርዓት ውስጥ

የያዙትን መልክና ይዘት ይዘው እንደሚገኙ እንገነዘባለን ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የኢሠፓን መመስረት ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶችን ሚና ፣ በአዲስ መልክ መመስረትና መዋቀር ፣ እንደዚሁም መንግሥት በአገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ሚና በአጠቃላይም ቀደም ሲል ያልነበሩ የሞያ ፣ የሠራተኛና የሕዝባዊ ድርጅቶችን ሚናና ሰፊው ሕዝብ በኢኮኖሚ ግንባታ ፣ በአገር መከላከያና በባህል ዕድገት ያሳየው ተሳትፎና ድርጅታዊ ጥንካሬ ስንመለከት የአዲሱ የፖለቲካ ስርዓት አካላት በመመስረትና በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውንና የፓርቲ አመራር ማግኘታቸውን እንገነዘባለን ፡፡ ይህ እንግዲህ የአሮጌውንና የአዲሱን የፖለቲካ ስርዓት በጣምራ መገኘትን ያሳያል ፡፡

ከቅድመ ካፒታሊስት የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ወደ ሶሺያሊዝም በሚደረገው ሽግግር ውስጥ የሚመሠረተው መንግሥት የሽግግር መንግሥት ነው ፡፡ ይህም መንግሥት የሰፊው ሕዝብ የጋራ የበላይነት የሚረጋገጥበት የሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው ፡፡

የዚህ መንግሥት ኢኮኖሚያዊ መሠረት የመንግሥትና የሕብረት ሥራ ማህበራት ይዞታዎች ገነው የሚታዩበት በአንፃሩ ደግሞ የተለያዩ የግብረት ይዞታዎች /ለምሣሌ ካፒታሊስት ፣ ወይም የግል ፣ የጥቃቅን ሸቀጣ ሸቀጥ አምራቾች ይዞታዎች የሚታዩበት ነው ፡፡

ከላይ የተጠቀሰው የፖለቲካ ስርዓት የተለያዩ የሶሺያሊስት የዕድገት ፈለገን የሚከተሉ ሀገሮች የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ካካሄዱ በኋላ ወደ ሶሺያሊስት ግምባታ የዕድገት ደረጃ ለመሸጋገር በሚያካሂዱት ሁለገብ አብዮታዊ ትግል ሂደት ውስጥ የሚመሠረት የፖለቲካ ስርዓት ነው ፡፡ የዚህ የፖለቲካ ስርዓት አንድ ጉልህና መሠረታዊ ባህሪይ የፖለቲካ ስርዓቱ መሪ ኃይል የሠርቶ አደሩ ፓርቲ መሆኑ ነው ፡፡ በዚህ ፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ፓርቲው የሚኖረው የመሪነት ሚና የሚታወቀው በመርህ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ መንግሥት ሕገ መንግሥት ውስጥም በጉልህ ይደነገጋል የዚሁ የፖለቲካ ስርዓት ድርጅታዊ አካሊት የሆኑት

መንግሥት ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ሌሎችም የመንግሥት የስልጣንና የአስተዳደር አካላት ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሚና እንደዚሁ በሀገሪቱ መንግሥት ሕገ መንግሥት ውስጥ በግልጽና በዝርዝር ይገለጻል ።

የዚህ የፖለቲካ ስርዓት ርዕዮተዓለማዊ መሠረት የማርክ ሲዝም ሌኒንዝም ርዕዮተዓለም ሲሆን ይህም በሀገሪቱ የውስጥና የውጪ ፖሊሲ ፣ በፓርቲው ድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ አመራር በሕዝባዊ ድርጅቶች አሰራርና አወቃቀር ፣ በመንግሥት የስልጣን አካላት አመሠራረትና አወቃቀር ፣ በሀገሪቱ የሕግና የፍትህ አስተዳደርና አፈጻጸም ፣ በመንግሥቱ የባህል ፖሊሲዎች ተግባ ራዊነት ውስጥ ይንፀባረቃል ።

ይህ ከቀደመ ካፒታሊስት የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ተነ ስተው የሶሺያሊስት የዕድገት ፈለግን በመከተልና ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን በማካሄድ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በሚመሠረቱ ሀገሮች ውስጥ የሚመሠረተው የፖለቲካ ስር ዓት በአራት መሠረታዊ የአሰራርና የአወቃቀር መርዕዎች ላይ የሚገነባ ነው ። እነዚህም የሰፊው ሕዝብ የነቃ ተሳትፎ ፣ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ፣ ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትና የሶ ሺያሊስት ሕጋዊነት መርዕዎች ናቸው ። የነዚህን መርሆዎች ምን ነት በሚመለከት ለወደፊት ሰፊ ውይይት የምናደርግ ስለሆነ እዚህ ላይ አናነሳቸውም ።

7.4 ሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት

ሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት በሠርቶ አደሩ መደብ የፖ ለቲካ የኢኮኖሚና የባህል የበላይነት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ስርዓት ሲሆን ኢኮኖሚያዊ መሠረቱም ሶሺሊስት የምርት ግንኙነት ነው ።

ሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት በሠርቶ አደሩ መደብ ፓርቲ ሁለገብ ድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ አመራር ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ስርዓት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ነው ።

የሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት መሠረታዊ ተግባሮች ብሔራዊ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው ሲሆን ከነዚህም የፖለቲካ ስርዓቱ ተግባሮች መካከል ዋናዎቹ፣

1ኛ. ለኮሚኒስት ሕብረተሰብ ግምባታ አስፈላጊውን ቁሳዊ፣ ቴክኒካዊና መንፈሳዊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣

2ኛ. በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትና በሶሺያሊስት አርበኛነት ላይ የተመሠረተ ሶሻሊስት የመከላከያ ኃይልን መመስረትና ማጠናከር ፣

3ኛ. የተሟላ ስብዕና ያለውና በኮሚኒስት ርዕዮተዓለም የታነፀ ሶሺያሊስት ሰው መፍጠርና ሶሺያሊስት ባህልን ማስፋፋት፣

4ኛ. የብሔሮችንና የብሔረሰቦችን የእናሳዎችን ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ እኩልነት በማረጋገጥ አንድ ወጥ የሆነ የተዋሀደ ሶሺያሊስት ሕብረተሰብ ፣

5ኛ. ለብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች ዲፕሎማሲያዊ፣ ፖለቲካዊ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ መስጠትና ለዓለም ሰላም በግምባር ቀደምትነት መታገል፣

6ኛ. በኢምፔሪያሊዝም ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄደው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ርዕዮተዓለማዊ ትግል ውስጥ በግምባር ቀደምትነት መሰለፍ ናቸው ።

ከሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት ጉልህ መገለጫዎች መካከል ዋናዎቹ ሰፊው ሕዝብ በኢኮኖሚ እቅድ አወጣጥና አፈጻጸም ፣ በመንግሥት የስልጣን አካላት አመሠራረትና አሰራር ፣ በፍትህና ሕግ አስተዳደር ፣ በማህበራዊ አገልግሎት ዘርፎች ፣ ገጠሬ መከላከያና ደህንነት ፣ በአዲስ ባህል ግምባታ የሚኖረው ሕጋዊ ተካትፎ ሲሆን እነዚህም የሕዝቡ የተካትፎ ዘርፎች የሶሺያሊስት ዲሞክራሲና የታቀደ የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ውጤቶች ናቸው ።

የሶሺያሊስት ስርዓት በውስጡ የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች አሉት ። እነዚህም የሶሺያሊስት ስርዓት ግምባታ ፣ የዳበረ

ሶሺያሊስት ስርዓት ደረጃዎች ሲሆኑ የሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት ተግባሮችም በዚሁ የሶሺያሊስት ግምባታ ሂደት ውስጥ እየዳበሩና እየሰፉ በመሄድ የወደፊቱን ኮሚኒስት ሕብረተሰብ እውን ለማድረግ የሚካሄዱትን ስራ ተግባሮች የሚያጠቃልሉ ናቸው ::
በዚህም ሂደት ውስጥ የሁሉም ሕዝቦች መንግሥት መመስረትና ለኮሚኒስት ስርዓት ግምባታ መፋጠን የሚደረገው ግሥጋሴ የሠርቶ አደሩ የበላይ ገዢነት ተግባራዊ ውጤቶች ይሆናሉ ::

እስካሁን ድረስ የፖለቲካ ስርዓት የዕድገት ደረጃዎች አንድ ባንድ እያነሳን ለማብራራት ሞክረናል ፣ እዚህ ላይ አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ማንሳት የሚገባን ይመስለናል :: ባሁኑ ጊዜ በአገራችን በመመስረት ላይ ያለው አዲሱ የፖለቲካ ስርዓት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል ? ምን ምን ተግባሮችን ያከናውናል ? እነዚህንና ሌሎችንም መሰል ጥያቄዎችን በማንሳት በሀገራችን በመመስረት ላይ ስለሚገኘው የፖለቲካ ስርዓት አንዳንድ አጠቃላይ ነጥቦችን በማንሳት እናብራራቸዋለን ::

8. <u>በአብዮታችን ሂደት ውስጥ ባገራችን ባሁኑ ጊዜ በመመስረት ላይ የሚገኘው የፖለቲካ ስርዓት ምን ይመስላል ?</u>

የማናቸውም የፖለቲካ ስርዓት ምሥረታ በአንድ ወቅት ብቻ የሚካሄዱት ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ክንዋኔዎች ውጤት አይደለም :: የአዲሱ የፖለቲካ ስርዓት ምሥረታ ከአዲሱ የፖለቲካ ስርዓት ዓላማ ጋር የማይጣጣሙ የአሮጌውን የፖለቲካ ስርዓት ዘርፎችን የማስወገድና የአዲሱን የፖለቲካ ስርዓት አካላትን የመመስረት ክንዋኔዎችን የሚያጠቃልል ውስብስብ ተግባር ነው ::

አዲሱ የፖለቲካ ስርዓት የሚመሰረተው በስከዛሬው ትግላችን በተቀዳጀናቸው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ድሎችና ለወደፊቱም በኢሠፓ መሪነት በምንቀዳጃቸው ድሎች ላይ ነው ::

በኢሠፓ መሥራች ጉባኤ ላይ በጓድ መንግሥቱ ኃይለማሪያም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ ፣ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበርና የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ

አዛዥ በቀረበው ሪፖርትና በኢሠፓ ፕሮግራም እንደዚሁም በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሶስተኛ መደበኛ ስብሰባ ሰነዶች ውስጥ እንደተጠቀሰው ሁሉ የሚመሠረተው የፖለቲካ ስርዓት የሽግግር የፖለቲካ ስርዓት ሲሆን የዚሁ የፖለቲካ ስርዓት አካል የሚሆነውም የሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የሽግግር መንግሥት ነው ። ይህ መንግሥት የሚቋቋምበትም ሕገ መንግሥት የሽግግር ሕገ መንግሥት ነው ።

ጓድ ዋና ፀሐፊው ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሶስተኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ እንደተጠቀሰው " ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በሪፐብሊክ አሃዳዊነት ላይ ተመሥርቶ በየደረጃው በሚያቋቁማቸው የመንግሥት የስልጣን አካላት አማካይነት የስልጣን ባለቤትነቱን ተግባራዊ ያደርጋል ።[17] ይህም በአዲሱ የፖለቲካ ስርዓት ምሥረታ ጥረታችን ውስጥ አንዱ ከፍተኛ እርምጃ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የተደራጀባቸው ሕዝባዊያን ድርጅቶች ከፖለቲካ ስርዓቱ ምሥረታ አኳያ በመጠናከር ላይ ስለሚገኙ በፖለቲካ ስርዓቱ ውስጥ የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ እየተጠናከረና እየሰፋ መጥቷል ። ቀደም እንደተጠቀሰው የዚህ ፖለቲካ ስርዓት ምሥረታ በመሪ ፓርቲያችን በኢሠፓ አመራር ሰጪነት የሚከናወን እንደመሆኑ ለዓላማችን ግብ መምታት ከወዲሁ አርግጠኞች ለመሆን ብንችልም በሪፐብሊኩም ሆነ ባጠቃላይ በፖለቲካ ስርዓቱ ምሥረታ ውስጥ የያንዳንዱ አብዮታዊ ዜጋ ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው ።

9. ማጠቃለያ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የፖለቲካ ስርዓትን ምንነት ፣ አመጣጥ፣ ባህሪያቶቹንና ተግባሮቹን እንደዚሁም የዕድገት ደረጃዎቹን በማመልከት አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦችን በማንሳት አብራርተናል ። እንደማናቸውም የማህበራዊ ስርዓት የፖለቲካ ስርዓት ቋሚና የማይለወጥ ሳይሆን ታዳጊ ፣ ተሸጋጋሪና ተንቀሳቃሽ ነው ።

ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ምሥረታ በተቃረብንበት ባሁኑ ወቅት የሪፐብሊኩን ምሥረታ በበለጠ ለማቃረብ እንዲቻል በየደረጃው የምናከናውናቸው ተግባሮች ውስጥ አመርቂ ውጤት ለማስገኘት የምንችለው የሪፐብሊኩን ምሥረታ በሚመለከት ያለንን ግንዛቤ በጋራም ሆነ በግል ለማስፋት ጥረት ስናደርግ ብቻ ነው ::

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሃሣቦች ለውይይቱ መነሻ ከመሆን አልፈው በርዕሱ ሥር የተጠቀሱትን ሃሣቦችና ጉዳዮች በሙሉ የሚያጠቃልሉ አይደሉም :: ስለሆነም በርዕሱ ላይ ያለንን ግንዛቤ ለማስፋት እንድንችል በኢሠፓ ፕሮግራም ፣ በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሰነዶች ላይ በመመስረት ተጨማሪ ጽሑፎችን በማንበብ ስለ ፖለቲካ ስርዓት የሚኖረንን ግንዛቤ ማዳበር አለብን ::

ጥያቄዎች

1. ፖለቲካ ማለት ምን ማለት ነው ?
2. የፖለቲካ ስርዓት ማለት ምን ማለት ነው ?
3. ከሌሎች የማህበራዊ ስርዓት አካላት ሁሉ የፖለቲካ ስርዓትን ዋይነተኛ የሚያደርገው ምንድን ነው ?
4. የፖለቲካ ስርዓት አካላት እነየቱ ናቸው ? በምሣሌ አስረዳ/ጂ/
5. የፖለቲካ ስርዓትን መሠረታዊ ባህሪያትን አመልክት/ቺ/
6. የፖለቲካ ስርዓት መሠረታዊ ተግባሮችን ጥቀስ/ሺ/
7. የካፒታሊስት የፖለቲካ ስርዓት ከሶሺያሊስት የፖለቲካ ስርዓት በምን በምን ረገድ ይለያያል ?
8. የሽግግር ወቅት የፖለቲካ ስርዓትን መሠረታዊ ባህሪያትና ተግባሮችን ግለጽ ::
9. በሶሺያሊስት መንግሥት ውስጥ የሠራተኛው ፓርቲ የፖለቲካ ስርዓቱ መሪ ኃይል ነው የሚባለው ለምንድን ነው ?
10. ባሁኑ ጊዜ በአገራችን ያለው የፖለቲካ ስርዓት ምን ዓይነት የፖለቲካ ስርዓት ነው ?
11. በካፒታሊስት የፖለቲካ ሥርዓትና በሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓት መካከል ያሉትን መሠረታዊ ልዩነቶች አስረዳ ::

1. Webesters Third New International Dictionary (Un abridged) Meriam Webester Pub. 1976. P. 1755
2. Fyodor Burlatsky, The Modern State and Politics. Progress Publishers, 1978, P. 16
3. V.I. Lenin, Collected Works, Vol 32 P. 83
4. Fyodor Burlatsky, P. 57
5. አምሳሉ አክሊሉና ኢ.ሲ.ቀዝባክ፣ እንግሊዝና አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ ገጽ 265.
6. Romould Fesinko, A System, Unpublished Material, Addis Ababa, 1985. P. 1
7. Alexander Spirkin, Dialectical Materialism Progress Publishers, Moscow, 1983. P. 97
8. Ibid.
9. Fyodor Burlatsky. P.48
10. Soviet Political Sciences Association, Political Systems: Development Trends: Moscow, 1979 No.77 P. 168
11. Fyodor Burlatsky, P. 49
12. Ibid.
13. Burlatsky, P. 49
14. Ibid.
15. በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ልዩ ፍርድ ቤት፣ ሕግና ፍርድ፣ ቅጽ 2 ቁጥር 2 ነሐሴ 1977 አዲስ አበባ ገጽ 61.
16. Burlatsky, P. 16
17. ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ፣ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበር፣ የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ለሦስተኛው የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ያቀረቡት ሪፖርት፣ ሠርቶ አደር ጋዜጣ ነሐሴ 27,1977፣ ቅጽ 6 ቁጥር 275 ገጽ 8.

በት. መ. ማ. ማ.ድርጅት ታተመ ።

Proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com